# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የማህበረሰብ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

**ኦሮማይ፣ ደራሲዉና ከአድማስ ባሻገር ልብ-ወለዶች የሴት**

**ገፀ ባህሪያት አሳሳልና ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንጻር ሲተነተን**

**በ ረድኤት እሱባለዉ**

**ግንቦት 2011ዓ/ም**

# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## ኦሮማይ፣ ደራሲዉና ከአድማስ ባሻገር ልብ ወለዶች የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳልና ከ እንስታዊነትፅንሰ ሀሳብ አንጻር ሲተነተን

በ ረድኤት እሱባለዉ

<u>የጥናቱ አማካሪ</u>፡- መምህር ሳራ መሀመድ (MA)

ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባቺለር ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ

ግንቦት 2011ዓ/ም

# የአማካሪው ማረጋገጫ

የጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴያትር ጥበባት ት/ት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማማከሪያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም ፊርማ

__________________ __________

ይህ በተማሪ ረድኤት እሱባለው ኦሮማይ ደራሲ እና ከአድማስ ባሻገር ልብ-ወለዶች የሴት ገፀ-ባህሪያት አሳሳል እና ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ሲተነተን በሚል የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርሲቲውን ጥራት ደረጃ ያሟላና ለቴአትር ጥበባት ት/ት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህ በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል።

አማካሪ ፊርማ

__________________ ____________

ፈታኝ 1 ፊርማ

__________________ ______________

ፈታኝ 2 ፊርማ

__________________ _____________

ቀን________________

## ምስጋና

በመጀመሪያ ለልዑል አግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይገባዋል። በመቀጠል ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት እድሉን ለሰጠኝ ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ፤ ምንም ሳትሰለች እዉቀት ምክር እና ጊዜዋን ለለገሰችኝ አማካሪዬ ወ/ ሮ ሳራ መሀመድ እንዲሁም ለደራሲ በአሉ ግርማ ምስጋናዬ የላቀ ነዉ።

## አበርክቶ

በሀገራችን  በጾታቸዉ ምክንያት ጥቃት ለደረሰባቸዉ ሴቶች በሙሉ መታሰቢያ ይሁንልኝ ፡፡

## አጠቃሎ

በልብ ወለድ ዉስጥ ገፀ ባህሪያት አምሳለ ሰብ ተደርገዉ ይሳላሉ። የገፀ ባህሪያት አሳሳሎች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ እና ሞራላዊ በመባል በአራት ይከፈላሉ። የሴት ገፀ ባህሪያት ከወንዶች ጋር በእኩልነት መሳል አለባቸዉ።ነገር ግን የበአሉ ግርማ ሶስት መፅሐፍቱ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያት በወንዶች እና በሚኖሩበት ማህበረሰብ ጥቃት የደረሰባቸዉ የተጨቆኑ እና ለበቀል የተነሳሱ ቆነጃጅት ናቸዉ። ስለዚህ የሴት ገፀ ባህሪያትን አሳሳል መተንተንና ከእንስታዊነት አንጻር መገምገም አስፈላጊ ነዉ።

የዚህ ጥናት አላማ ኦሮማይ ፣ ደራሲዉ እና ከአድማስ ባሻገር በተሰኙት ልብ-ወለዶች ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገጸ ባህሪያት  አሳሳል እና ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻር መተንተን ሲሆን አይነታዊ በተለይም ገላጭ የምርምር ዘዴን መሰረት በማድረግ እንዲሁም መጽሀፍትን፣ ጥናታዊ ጽሑፎችን ፣መፅሔቶችን እና ጋዜጣወችን በማንበብ ፤ የተለያዩ ሰወችን በማማከር መረጃ ተሰብስቧል።

ኦሮማይ፣ ከአድማስ ባሻገር እና ደራሲው ልብ ወለድ ላይ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያት በጥሩ ሁኔታ ተስለዋል። ቢሆንም ግን ከወንድ ገጸ ባህሪያት አንጻር በቁጥርም ሆነ በተሰጣቸዉ ሚና ዝቅ ተደርገዋል። ስነጥበብ ለሰው ልጅ ስሜት ቅርብ በመሆኑ ደራሲዎቻችን ለእንስታዊነት ፅንስ ሀሳብ ትኩረት ሰጥተዉ የጾታ እኩልነትን የሚያሳዩ ስራዎችን በመስራት ማህበረሰቡ ያለውን የተሳሳተ ጾታ አመለካከት እንዲቀየር ቢያስተምሩ መልካም ነዉ።

# ማውጫ

**አርዕስት** **ገፅ**


የአማካሪው ማረጋገጫ 3

ምስጋና 3

አበርክቶ 4

አጠቃሎ 5

ምህንጻረ ቃላት 8

ምዕራፍ አንድ 9

1. መግቢያ 9

1.1. የጥናቱ ዳራ 10

1.2.ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች / የጥናቱ መላምት 11

1.2. የጥናቱ አላማ 11

1.2.1. አብይ አላማ 11

1.2.2. ንዑስ አላማዎች 11

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታዎች 11

1.4. የጥናቱ ወሰን 12

1.5. የጥናቱ ዘዴ 12

1.6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 12

1.7. የጥናቱ አወቃቀር 12

ምዕራፍ ሁለት 13

2.1. ክለሳ ድርሳን 13

2.1.1. ልብ ወለድ ምንድን ነዉ 13

2.1.2. ገፀ ባህሪ ምንድን ነዉ? 14

2.1.3. የገፀ ባህሪ አሳሳል ደረጃ 14

2.1.4. የእንስታዊነት ምንነትና አመጣጥ/ አጀማመር 16

2.2. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት 19

ምዕራፍ ሶስት 20

3.1. ኦሮማይ ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ 20

3.2. ደራሲው ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ 21

3.3. ከአድማስ ባሻገር ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ 23
3.4. የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና 24
3.4.1.ኦሮማይ የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና 24
3.4.2. ደራሲው የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና 27
3.4.3. ከአድማስ ባሻገር የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ትንተና 34
3.5. ከእንስታዊነት ጾንስ ሀሳብ አንጻር ትንተና 36
3.5.1.ኦሮማይ ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና 36
3.5.2. ደራሲው ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና 38
3.5.3. ከአድማስ ባሻገር ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና 39
ምዕራፍ አራት 41
4.1. ማጠቃለያ 41
4.3. ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ 43

# ምህንጻረ ቃላት

ዓ/ምፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌዓመተ ምህረት

እ.ኤ.አ ፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌ..እንደ ኤሮፓዊያን አቆጣጠር

ክ/ዘመን ፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌክፍለ ዘመን

ዩ.ኤስ.ኤፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌፌዩናይትድ እስቴት ኦፍ አሜሪካ

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

በአንድ ልብ-ወለድ ዉስጥ ታሪክን የሚገልጽ የጀርባ አጥንት ገጸ ባህሪ ነዉ። ገፀ ባህሪያት ስጋ ለብሰዉ ባህሪ ተጎናጽፈዉ በሰዉ አምሳል የተፈጠሩ የሚኖሩና የሚሞቱ የገሀድ አለም ነፀብራቆች ናቸዉ። እንዲሁም መጠሪያ ተሰጥቷቸዉ፣ መኖሪያ ተበጅቶላቸዉ የሚበሉ፣የሚጠጡ ፣የሚንቀሳቀሱ፣ የሚናገሩ፣ የሚተነፍሱ፣ የሚኖሩ እና የሚሞቱ ፣የአንድን ቦታና ዘመን ልምድን የሚያንጸባርቁ አምሳለ ሰብ ተደርገዉ ይሳላሉ።

የገጸ-ባህሪያት አሳሳል አራት ደረጃዎች አሉት። እነሱም አካላዊ የገጸ-ባህሪ አሳሳል ፣ማህበራዊ የገጸ-ባህሪ አሳሳል ፣ ስነ ልቦናዊ የገጸ-ባህሪ አሳሳል እና ሞራላዊ የገጸ-ባህሪ አሳሳል ናቸዉ። ጠቅለል ተደርገዉ ሲታዩ አካላዊ ገጽታና ህሊናዊ ገጽታ ተብለዉ በሁለት ይከፈላሉ ። ማህበራዊ ፣ስነ ልቦናዊ እና ሞራላዊ አሳሳሎች ህሊናዊ ወይም ዉስጣዊ ገጽታዎች ሲሆኑ አካላዊ ገፅታ ደግሞ የዉጭ ወይም አፋዊ የሆነዉን አሳሳል ይገልፃል።

እንስታዊነት ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት ግዴታ እና ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ እንዲሁም በማህበረሰቡ ዉስጥ ሊኖራቸዉ ስለሚገባ ነጻነት የሚታገል ንቅናቄ ሲሆን እኤአ በ19ኛዉ ክ/ዘመን ተጀምሯል።

በዚህ መሰረትም ይህ ጥናት በበአሉ ግርማ በተለያየ ጊዜ የተፃፉ ኦሮማይ ከአድማስ ባሻገር እና ደራሲዉ በተባሉ ልብ ወለድ መጽሀፍት ላይ ተደጋጋሚ የገጽ ንባብ በማድረግ የሴት ገጸ ባህሪያትን አሳሳል ይተነትናል ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻርም ይገመግማል ።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

እንስታዊነት ሴቶችን በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ዘርፎች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ የተጀመረ እንቅስቃሴ ነዉ። የሴት ገፀ ባህሪያት ከወንዶች ጋር በእኩልነት መሳል አለባቸዉ።

ሴቶች በአንድ ማህበረሰብ ብሎም በአለም ላይ የሚያበረክቱት አስተዋጾ ሰፊ ቢሆንም ብዙ ጊዜ በእዉኑ ሆነ በስነ-ፅሁፉ አለም በልምድና በባህል ምክንያት ታፍነዉ ወደ ኃላ ሲቀሩ እንመለከታለን። አጥኝዋ ለዚህ ጥናት ያንሳሷት ምክኒያቶች ዉስጥ የመጀመሪያዉ የበአሉ ግርማ ሶስት ልብ ወለድ መፅሐፍቱ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያት በወንዶች እንዲሁም በሚኖሩበት ማህበረሰብ ጾታዊ ጭቆናወች የደረሰባቸዉ እና ለበቀል የተነሳሱ ቆነጃጅት ብቻ መሆናቸዉ ሲሆን። በተጨማሪም ሴት እንደመሆኔ ሴቶች በሁሉም መስክ ከወንዶች እኩል ቢሰማሩ ስኬታማ እና የተሻለ ስራን እንደሚሰሩ ስለማምን ነዉ።

ሁለተኛዉ ምክንያት ደግሞ ሴቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ መሆን ሲገባቸዉ በኦሮማይ ፣ ከአድማስ ባሻገርና ድራሲዉ ልብ ወለዶች ዉስጥ ሴቶች በቁጥር እንዲሁም በተሳትፎ ዝቅ ተደርገዉ መሳላቸዉ ነዉ፡፡

ሌላዉ ምክንያት  በነዚህ መጽሐፍት ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገፀ ባህሪያትን አሳሳል አንጻር እንዴት ተስለዋል የሚለዉን ለማሳየት ነዉ፡፡

## 1.2.ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች / የጥናቱ መላምት

ይህ ጥናት የተለያዩ መሰረታዊ የሆኑ ጥያቄወችን ወይም መላምቶችን ያነሳል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ በልብ ወለድ ዉስጥ ሴት ገጸ ባህሪያት እንዴት እና በምን መልኩ ተስለዋል፤ የሴት ወይም የወንድ ሀላፊነት ተብለዉ የተቀመጡ ስራዎች አሉ ወይ ፤ የወንድ የበላይነት በምን መልኩ ተገልጾል እንዲሁም ገጸ ባህሪያት አሳሳል ስልጣኑ በማን ላይ ነዉ የሚሉትን ያካትታል፡፡

### 1.2. የጥናቱ አላማ

### 1.2.1. አብይ አላማ

- ኦሮማይ ፣ደራሲዉ እና ከአድማስ ባሻገር በተሰኙት ልብ-ወለዶች ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገጸ ባህሪያት  አሳሳል እና ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻር መተንተን ፡፡

### 1.2.2. ንዑስ አላማዎች

- ኦሮማይ በተሰኘ ልብ-ወለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገጸ ባህሪያት  አሳሳል አንጻር መተንተን ፡፡
- ደራሲው በተሰኘ ልብ-ወለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገጸ ባህሪያት  አሳሳል አንጻር መተንተን፡፡
- ከአድማስ ባሻገር በተሰኘ ልብ-ወለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከገጸ ባህሪያት  አሳሳል አንጻር መተንተን፡፡
- ኦሮማይ ፣ደራሲዉ እና ከአድማስ ባሻገር በተሰኙት ልብ-ወለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያትን ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻር መገምገም፡፡

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታዎች

- ለማህበረሰቡ ስለ ጾታ እኩልነት ግንዛቤ እንዲፈጠር የአመለካከት ለዉጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
- ደራሲዎች የእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ ላይ ትኩረት እነዲሰጡ ያመላክታል ፡፡

- የልብ ወለድ አንባቢወችን የእዉቀት ክፍተት ለመሙላት ያስችላል፡፡
- ለሌሎች አጥኚዎች እንደ መነሻ ወይም ማጣቀሻነት ያገለግላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

አጥኝዋ ትኩረት አድርጋ የምትሰራዉ ኦሮማይ፣ ደራሲዉ እና ከአድማስ ባሻገር በተሰኙ ልብ ወለድ መጽሀፍት ዉስጥ የሚገኙ ሴት ገጸ ባህሪያትን ከአራቱ የገጸ ባህሪያት አሳሳል አንጻር መተንተን በተጨማሪም ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻር መገምገም ይሆናል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

የጥናታዊ ፅሁፎች ምርምር አይነታዊ ምርምር እና መጠናዊ ምርምር በመባል በሁለት ይከፈላል፡፡ ይህ ጥናትም አይነታዊ የምርምር ዘዴ በተለይም ገላጭ የምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ በቅድሚያ የተመረጡ ልብ-ወለዶችን  በተደጋጋሚ በማንበብ  የሴት ገፀ-ባህሪያትን አሳሳል የገጽ ንባብ ትንተና ላይ በመመስረት ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር ለማሳየት ይሞክራል፡፡

ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ የተለያዩ መጽሀፍትን፣ የታተሙ ጥናታዊ ጽሆፎችን ፣መፅሄቶችን እና ጋዜጣወችን በማንበብ  እንደ ማጣቀሻነት በማቅረብ መረጃን ለመሰብሰብ ይሞክራል፡፡

## 1.6. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አብዛኛዎቹ ጥናቶች ልብ ወለድ ላይ ያሉ ሁሉም ገፀ-ባህሪያት ላይ በመሰራታቸዉ በሴቶች ላይ ብቻ ባለማተኮራቸዉ ምክኒያት የማጣቀሻ ፅሁፎች ችግር  አጋጥሞኛል ፡፡የጊዜ እጥረትም ሌላዉ ችግር ነዉ፡፡

## 1.7. የጥናቱ አወቃቀር

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች ይከፈላል፡፡ ምዕራፍ አንድ ላይ መግቢያ፣የጥናቱ ዳራ፣የጥናቱ አላማዎች፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱ ወሰን፣የጥናቱ ዘዴ፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የጥናቱ አወቃቀር ይካተታሉ፡፡ ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳናት እና የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝትን ሲይዝ በሶስተኛዉ ምዕራፍ ደግሞ የተገኙት መረጃዎች ይተነተናሉ፡፡ ማጠቃለያ፣ የመፍትሔ ሀሳብ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ እና  ዋቢ መጽሐፍትን  በመጨረሻዉ ምዕራፍ ያስቀምጣ

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1. ክለሳ ድርሳን

### 2.1.1. ልብ ወለድ ምንድን ነዉ ?

ስለ ልብ ወለድ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ወይም ብያኔ መስጠት አዳጋች ቢሆንም ብዙ የስነ ፅሁፍ ሀያሲያን እና ደራሲያን የተለያዩ ሀሳቦችን ሰጥተዋል፡፡ አማረ ማሞ የልብ ወለድ ድርሰት አጻጻፍ በተሰኘ መጽሐፉ “ልብ ወለድ ድርሰት የምንኖርበትን ዓለም የሒወት ዉጣ ዉረድ የሚያሳየን መስታዉት ነዉ፡፡” (1957:17) በማለት ሲያስቀምጥ፡፡ ዘሪሁን አሰፋ ደግሞ “ልብ ወለድ የግለሰባዊና ማህበራዊ ህይወት ልዩ ልዩ ገፅታወች የሚንፀባረቁበት በቃላት አማካኝነት የሚሳል ምናባዊ የሆነና በዉል የሚታይ ነፍስ ያለዉ ስዕል ነዉ፡፡” (2007:53) በማለት ከተለያዩ ብያኔዎች ጋርም በማዛመድ ገልጾታል፡፡ ከነዚህ ጽሁፎች የምንረዳዉ ልብ ወለድ በእዉኑ አለም የሚኖሩ ሰዎችን አጠቃላይ የሰዉነት ባህሪ እና ስራዎችን እዉነት አስመስሎ የሚቀርብ የስነ ፅሁፍ አይነት እነደሆነ ነዉ፡፡ ልብ ወለድ ከደራሲዉ ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰዉ ልጅን ደስታ ፣ ሀዘን፣ችግር፣ ማግኘት እና ማጣት በአጠቃላይ የሒወትን ዉጣ ዉረድ የሚያሳይ የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ነዉ፡፡ በልብ ወለድ ዉስጥ ያሉ ታሪኮች በእዉነት አለም ያልተፈፀሙ ነገር ግን በደራሲዉ ምናብ የተፈጠሩ ሊሆኑም ይችላሉ፡፡

### 2.1.2. ገፀ ባህሪ ምንድን ነዉ?

ገፀ ባህሪያት ልክ በእዉኑ አለም እንዳለ ሰዉ ስጋ ለብሰዉ የራሳቸዉ የሆነ ተግባር ተሰቷቸዉ ደራሲዉ ሀሳቡን የሚያስተላልፍባቸዉ ተወካዮች ናቸዉ፡፡ የልብ ወለድ ገጸ ባህሪያት አንዳንዴ እንደ ትክክለኛ ሰዎች እንዳለ ከነ ሙሉ ማንነታቸዉ ወይም በከፊል ማንነታቸዉ ላይ መሰረት በማደርግ ሊቀረፁ ይችላሉ፡፡ ዋናዉ ነገር በደራሲዉ አማካኝነት የልብ ወለድ ታሪክና ሴራን ተሸክመዉ የሚጎዙ ሰዎች እንስሳት ወይም ግዑዝ አካላት መሆናቸዉ ነዉ፡፡ገጸ ባህሪያት ሰዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ሚካኤል ልዑል ሰገድ የፊልም ጽሁፍ በሚል መፅሐፉ ላይ “ገፀ ባህሪ ሲባል በታሪክ ዉስጥ ተስለዉ የሚገኙ ሰዎች ለማለት ሲሆን እንሰሳት ግኡዝ ነገሮች መንፈሳዊ ፍጡራን ረቂቅ ሀሳቦችም እንደ ገፀ ባህሪ ይቆጠራሉ ”(2006:29) ሲል አብራርቷል፡፡

### 2.1.3. የገፀ ባህሪ አሳሳል ደረጃ

ገፀ ባህሪያት የገሀዱ አለም ነጸብራቅ እንደመሆናቸዉ መጠን ደራሲዉ መልእክቱን ለተደራሲዉ የሚያስተላልፈዉ በገጸ ባህሪያት ህሊናዊና አካላዊ ማንነት ላይ በመመስረት ነዉ፡፡ድራሲዉ ሰዎችን ወይም

ግኡዝ ነገሮችን በገጸ ባህሪ መልክ ሲገልጻቸዉ አንባቢዉ የሚረዳዉ የገሀዱን አለም ሰዎች እና ባህሪያቸዉ መሆኑን ነዉ። የገፀ ባህሪ አሳሳል ደረጃዎች አካላዊ ፣ማህበራዊ፣ስነ ልቦናዊ እና ሞራላዊ በመባል ይከፈላሉ። ስለዚህ በምናባዊ ስራ ጊዜ ገፀ ባህሪያት በአራት ዋና ዋና የገፀ ባህሪያት አሳሳል ዘዴወች መሰረት መፈጠር አለባቸዉ።

## 2.1.3.1. አካላዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ

አካላዊ የአሳሳል ደረጃ የምንለዉ የገጸ ባህሪዉ የዉጫዊዉ ማንነት ሲሆን ከአራቱ የገፀ ባህሪያት አሳሳሎች ቀላሉ ነዉ ተብሎም ይታሰባል።ስለ ማጠር መርዘም መቅላት መጥቆር መልከ ግቡነት መልከ ጥፉነት መቅጠን መወፈር የጸጉር ሉጫነት ከርዳዳነትና ሸበት ፂም እና አለባበስ ስለ ሁሉም አካላዊ ወይም ዉጫዊ ነገር ጥልቀት ያለዉ መረጃን የምናገኝበት ትንተና ነዉ። ደበበ ሰይፉ የቲያትር ጥበብ ከጽሀፈ ተዉኔት አንጻር በሚል መጽሀፉ እንዲሀ ብሏል

> ‹‹ጸሀፊዉ የሚቀርጻቸዉ ገፀ ባህሪያት በተደራሲዉ አእምሮ የሚታመኑ
> መሆን አለባቸው። ገፀባህሪያት በተለያየ ገቢር የተለያየ መልክ ሊኖራቸ
> ው አይገባም። በሚቀጥለው ገቢር ለውጥ እንዲኖራችው የሚያስፈልግ
> ሲሆን እንደፈረሰኛ ውሀ ድንገት ደራሽ ሆኖ የተደራሲያኑን ግምት
> በሚዳጭ መንገድ ሳይሆን በቀዳሚው ገቢር ይህንኑ ለውጥ የሚጠቁ
> ሙ ምክንያታዊ ምንጮች ፀሀፊ ተውኔቱ ካስቀመጠ በኋላ ቢሆን ጥሩ
> ነው።››(28፡1973)

በመሆኑም ደራሲዉ የገጸ ባህሪያቱ አካላዊ ማንነት ላይ ትኩረት በማድረግ ለተደራሲዉ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት አለበለዚያ ስራዉ ትርጉም አልባ ይሆናል።

## 2.1.3.2. ማህበራዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ

ማህበራዊ የአሳሳል ደረጃ የምንለዉ አንድ ገጸ ባህሪ ከማህበረሰቡ ጋር የሚኖረዉ መስተጋብር ባህል የሀይማኖት አቋም ሀብት ቤተሰባዊ ሚና እና ያለዉ ግንኙነት የስራ ሁኔታዉን እና በማህበራዊ ኑሮ ዉስጥ ያለዉን አዎንታዊና አሉታዊ ሚናዉን የምንረዳበት ነዉ። በዚህ አሳሳል ደረጃ ማህበራዊ ተግባራቸዉ ምን ድረስ እንደሆነ እና ስኬትና ድክመቶቻቸዉን እናይበታለን ። ከተቃራኒ አቻቸዉ ጋር ያላቸዉ ግንኙነት ከትክክለኛ ህይወት

ሳይርቁ የገሀዱ አለም ግልባጭ ተደርገዉ መሳል ይኖርባቸዋል ።

### 2.1.3.3. ስነ-ልቦናዊ የገፀ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ

በዚህ የአሳሳል ደረጃ የገጸ ባህሪያዉን የዉስጥ ስሜት የምናጤንበት ትኩረቱን ወይም አስተዋይነቱን ለነገሮች ያለዉን ፍላጎት ለመስጠትና ለመቀበል የሚጠቀመዉ እዉቀት ፍቅር እና ጥላቻ መከፋትና መደሰት የምንረዳበት የአሳሳል ዘዴ ነዉ። ፋንታሁን እንግዳ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ በተሰኘው መፅሀፍ እንዲህ ሲል ይገልፃል። ‹‹ስነ ልቦናዊ የአሳሳል ደረጃ በጭንቅላት ውስጥ ተውጠንጥነው ለውጫዊው አለም ይፋ የሚሆኑትን ስሜታዊነትና አስተዋይነትን ሁሉ በመቅረፅ የየገፀባህሪያቱ ህሊናዊ መልክ የሚታይበት መንገድ ነው።፟፟፟ (2005፡28)

### 2.1.3.4. ሞራላዊ (ግብረ-ገባዊ) የገፀ ባህሪያት አሳሳል ደረጃ

ይህ የአሳሳል ደረጃ ገጸ ባህሪዉ በታሪኩ ዉስጥ ያለዉን የክብርና የዉርደት ደረጃ የሚያሳይ ሲሆን የገጸ ባህሪዉ ስብዕና ጉረኝነት ወይም ትህትና መሸነፍ ወይም ድል ማድረግ ታላቅነት ወይም ታናሽነት የሚሳልበት ህፀፅ ወይም ጉድለት የሚመዘዝበት የአሳሳል ደረጃ ነዉ። ገጸ ባህሪያት ሲሳሉ ጎልተዉ የሚታወቁበት እና የሚሰጣቸዉ ሞራላዊ ደረጃዎች በሰዎች  ዘንድ ያላቸዉ ተቀባይነት ዝቅ ያለ ወይስ ከፍ ያለ ነዉ የሚለዉን የሰዉን ዉስብስብና አስቸጋሪ ጸባይ ስነ ምግባራዊ አሳሳላቸዉ የአንባቢዉን መልስ መሻት የጥያቄዉን ቁልፍ የሚፈታ ነዉ።ፋንታሁን እንግዳ የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ በተሰኘው መፅሀፉ‹‹የሞራልን ጉዳይ እንደ አብይ ነገር በመውሰድ ገፀ-ባህሪያቱን የሞራል ባለቤት ወይም የሞራል ድሀ አድርጎ መቅረፅ በተለይ ለታምራዊ በግብረገባዊ የሀይማኖት ተውኔቶች የተለመደ የአፃፃፍ ስልት ነው።፟፟(2005፡29)

## 2.1.4. የእንስታዊነት ምንነትና አመጣጥ/ አጀማመር

### 2.1.4.1. . የእንስታዊነት ምንነት

አባታዊ አገዛዝ ስርአት (patriarchy) የወንዶች የበላይነት የሰፈነበት ነዉ። ከትዉልድ ትዉልድ እየተወራረሰ የወንዶችን ጨቆኝነት ትክክልና ተገቢ አገዛዝ እንደሆን በማሳመን በማህበረሰቡ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አሳድሯል።ኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ላይ እንደተቀመጠዉ አባታዊ አገዛዝ ስርአት (patriarchy) ማለት ፟፟አባት ወይም የቤተሰብ ትልቅ የሆነ ወንድ ቤተሰቡን ሆነ ዘር ማንዘሩን ባሰበዉ መንገድ የሚያስተዳድርበት እና የቤተሰቡ ራስ የሚሆንበት የማህበረሰብ አገዛዝ ስርአት ነዉ ይላል።፟፟1) ይህ አገዛዝ የሰዉ ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ የነበረ ነዉ። አብዛኛዉ ማህበረሰብም ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንደሆነ ያምናል።በመጽሀፍ ቅዱስ ላይም ይህን ሀሳብ የሚደግፉ አስተምሮቶችን እናገኛለን። ለምሳሌ በመጽሀፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ

ሶስት ቁጥር አስራ ስድስት ላይ ቈወለድሽ በኋላ ፈቃድሽ ወደ ባልሽ ይሆናል እሱም ይገዛሻል ቈ(ዘፍ 3፡16) የሚል ጥቅስ እናገኛለን ይህም ሴት ልጅ በባልዋ አገዛዝ ስር እንደሆነች የሚያስተምር ነዉ፡፡

እንስታዊነት በተለያየ ጊዜና ቦታ የተለያዩ ትርጎሜዎች ተቀምጠዉለታል፡፡ የኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ‹‹እንስታዊነት ማለት በፆታ እኩልነት መሰረተ ሀሳብ ላይ የሴቶችን መብት የሚደግፍ ነዉ፡፡ቈ2) ብሎ ያስቀምጣል፡፡ እንዲሁም Elinore Burkt ሴቶች በፆታቸዉ ብቻ የሚያጋጥማቸዉን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ገልፃ ‹‹እንስታዊነት በማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ የፆታ እኩልነት ማመን ቈ(3) እንደሆን Britanica article በተባል ድረ ገፅ ላይ ባሳተመችዉ ጥናታዊ ፅሁፍ አብራርታለች፡፡

## 2.1.4.2. የእንስታዊነት አመጣጥ/ አጀማመር

የእንስታዊነት እንቅስቃሴ በአለም ላይ በአፍሪካ እንዲሁም በሀገራችን ኢትዮጵያ ረጅም የሆነ አመጣጥና እድገት አለዉ፡፡ ነገር ግን መች እንደተጀመረ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ በ19ኛዉ ክ/ዘመን እና በ20ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በአሜሪካና ብሪታኒያ በሴቶች መብትና ጥቃት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ የተደረገ ሲሆን ከፍተኛ የሆነ ድጋፍንም አግኝቷል፡፡

የእንስታዊነት እንቅስቃሴ በሶስት የተለያዩ ጊዜያት ተከፍሎ ይታያል፡፡ የመጀመሪያዉ እንስታዊነት እንቅስቃሴ በ19ኛዉ ክ/ዘመን የተጀመረ ሲሆን በህግ ፊት ያለን የእኩልነት መዳከም በተለይም በሴቶች ተጠቂነት ላይ ያተኮረ እንቅስቃሴ የታየበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ የእንቅስቃሴ ዘመን በዩ.ኤስ.ኤ በ1848 ዓ/ም በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴቶችና የወንዶችን እኩልነት ለማረጋገጥ *ሁሉም ሰዉ እኩል ነዉ* የሚል የነጻነት አዋጅ ታዉጆም ነበር፡፡

ሁለተኛዉ የእንቅስቃሴ ምዕራፍ ከ1960-1980ዎቹ የነበረ ሲሆን በአንድ ማህበረሰብ ዉስጥ በባህል ምክንያት ከጾታ ጋር ተያይዘዉ ሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች እና ጾታዊ አድሎ ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር፡፡ ፌሚኒን ሚስቲክ በሚል ርዕስ ቤቲ ፈሪደን በተባለች ጸሀፊ የታተመ መጽሀፍ በ1960ዎች አጋማሽ የሴቶችን የቤት ዉስጥ እና ልጅን የመንከባከብ ስራወችን ብቻ መስራትን በመገምገም በአለም ላይ ትልቅ ተጽንኦ በማሳደር ፍትሀዊና ትክክለኛ የቤት ዉስጥ የስራ ድርሻ እንዲኖር አድርጓል፡፡

በሁለተኛዉ እንቅስቃሴ ወቅት የነበሩ ችግሮችን በማረምና ሌሎች በርካታ ጾታዊ ጉዳዮችን በማካተት ከ1990-2000ዓ/ም ሶስተኛዉ የእንስታዊነት እንቅስቃሴ የቀጠለ ሲሆን ዋና ዋና ሀሳቦቹም ሴቶች በመጀመሪያ ሁለተኛና በኮሌጅ ትምህርቶች ስኬታማ ሆነዉ እዉቀታቸዉን በተለያየ መንገድ እንዲያበረክቱ አራሳቸዉን ማስተዳደር እንዲችሉ ፖለቲካዊ ዉሳኔዎች ላይ እንዲሳተፉ፣ በጋብቻና ልጆች ሁኔታም በነጻነት መወሰን እንዲችሉ እንዲሁም የማህበረሰቡ ወግና ልማዳዊ አሰራሮች ለሴቶች የተመመቹ እንዲሆኑ ማድረግ ናቸዉ፡፡

በኢትዮጵያ የእንስታዊነት እንቅስቃሴ የተለያየ ታሪክ አለዉ ፖሚ አያሌዉ የተባለች የሴቶች መብት ተከራካሪ

እንዲሁም የፖለቲካ ባለሙያ ባሳተመችዉ ጥናታዊ ጽሁፍ እንቅስቃሴዉ በኢትዮጵያ በ1930 ዓ/ም እንደተጀመረ ትገልጻለች። በሴቶች ላይ የሚደርሱ መጠነ ሰፊ ችግሮች ለረጅም ጊዜ ትኩረት እንዳልተሰጣቸዉ በመገንዘብ በ1991 ዓም ኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ተመሰረተ ለሴቶችየህግ አገልግሎቶችን መስጠት ጀመረ። ከዚህ በመቀጠል ❝ሴታዊት❞የተባለ በሁለት ኢትዮጲያዉያን የተከፈተ ማህበር ሴቶችን ከወንዶች በኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ በፖለቲካዊ ዘርፎች እኩል ለማድረግ በማህበርሰቡ ሴቶች ላይ የሚደርሱ እንደ መገረዝ የመሳሰሉ ጎጅ ልማዳዊ ድሪጊቶችንና ቤት ዉስጥ እና ዉጭ የሚፈጸምባቻወን የመደፈር የመደብደብ የመሰደብ የስራ መብዛት እና የመሳሰሉ አካላዊና መንፈሳዊ ጥቃቶችን ለመቀነስ ስራዎች ተሰርተዋል። የሴቶችን ጾታዊ እኩልነት ማረጋገጥ ቀላል ባይሆንም ሴቶች ላይ ስለሚደርሱ በደሎች ትምህርትን በመስጠት እና ድርጊቱን በመከላከልን ❝ቀይ ቀሚስ❞የተባለ ዘመቻም ነበረ።

### 2.1.4.3. እንስታዊ ስነ ጽሁፍ (litreary feminism)

እንስታዊ ስነ ጽሁፍ የእንስታዊነት እንቅስቃሴን ተከትሎ የመጣ ሲሆን በስነ ጽሁፍ ዙሪያ ሴቶች ስለሚኖራቸዉ ሚናና የሴት ገጸ ባህሪያት ስለሚሳሉባቸዉ መንገዶች የሚያስገነዝብ ንቅናቄ ነዉ። በመሰረታዊነት ሃሳቡ በሁለተኛዉ የእንስታዊነት እንቃስቃሴ ወቅት በ1960 ዓ/ም ተጀምሯል።ትኩረቱም በዋናነት ሴቶች በአባታዊ አገዛዛ ጊዜ ከትምህርት እና ፖለቲካ ስራ ጋር የተያያዘ የሚደርስባቸዉ ችግር ላይ ነዉ።

## 2.2. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

አጥኝዋ ከዚህ ጥናት ርዕስ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸዉ በርካታ ለዲግሪ ማሟያነት የተሰሩ እና ሌሎች ፅሁፎችን ለመቃኘት እንደሞከረችዉ ከጥናቱ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸዉ ፅሁፎችን ተመሳስሎ እና ልዩነት ለናሙናነት እንደሚከተለዉ አቅርባለች።

ዮናስ እንዳልካቸዉ ሰኔ 2010 ዓ/ም ❝ዋና ዋና ገፀ ባህሪያት ትንተና በባዶ እግር ተዉኔት❞በሚል ርዕስ ለጎንደር ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ያቀረበዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ጽሁፍ ጋር የሚያመሳስለዉ ሁለቱም ገጸ ባህሪያትን በአራቱ የገጸ ባህሪ አሳሳል ደረጃ መተንተናቸዉ ሲሆን ልዩነታቸዉ ደግሞ ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ ልብ ወለድ ላይ ባሉ ሴት ገጸ ባህሪያት የተሰራ ሲሆን ያኛዉ ደግሞ ተዉኔት ላይ ያሉ ዋና ዋና ገጸ ባህሪያትን ይተነትናል።

እንዲሁም ካቢኒ መኮነን ሰኔ 2001 ዓ/ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ጥናት ተቋም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ❝ገጸ ባህሪ አሳሳል በየጠፍ ከዋክብት ረጅም ልቦለድ❞በሚል ርዕስ ያቀረበዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ከዚህ ስራ ጋር የሚያመሳስለዉ የልብ ወለድ ገጸ ባህሪ አሳሳል ላይ መሰራቱ እና ገላጭ የምርምር ዘዴን መጠቀሙ እንዲሁም የጥናቱ አደረጃጀት በአራት ክፍሎች መሰራቱ ነዉ። ነገር ግን ሁሉም ገጸ ባህሪያቱን ጠቅለል ባለ መንገድ በአካላዊና ህሊናዊ የአሳሳላ ደረጃዎች ብቻ ሲተነትን ይህ ጥናት

ደግሞሴት ገጸ ባህሪያትን ብቻ በአራት አሳሳል ደረጃዎች በስፋት ያብራራል፡፡

ሌላዉ ተመሳሳይ ስራ ሩቢና ማንዶካል‹‹ፌሚኒስት ክሪቲክ ኦፍ ዘ ካራክትር ዴዝዴሞና ኢን ሼክስፔርስ ኦቴሎ›› ብሎ እኤአ በ2015 ያሳተመዉ ጥናታዊ ስራ ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመደዉ ሴት ገጸ ባህሪን ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር በመገምገሙ ነዉ፡፡ ይህ ስራ በቴአትር ላይ መሆኑ እና አንድዋን ሴት ገጸ ባህሪ ብቻ መተንተኑ ደግሞ ልዩነታቸዉ ነዉ፡፡

በ ጃካርታ እኤአ በ 2010 ዓ/ም ‹‹አን አናላይሲስ ኦፍ ዘ ሜይን ካራክተር ስሮው ፌሚኒዝም አፕሮች ኢን ዘ ኖብል ሉቺያ ሉቺያ ባይ አድሪያን ትሪጋኒ ››በሚል ርእስ ኑሪ አቲቃህ ለዲግሪ ማሟያነት የሰራዉ ጥናት ልብ ወለድ ላይ በመሰራቱ እንዲሁም የሴት ገጸ ባህሪያትን ከእንስታዊነት እሳቤ አንጻር በመተንተኑ ከዚህ ጥናት ጋር በሰፊዉ ይመሳሰላል ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1. ኦሮማይ ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ

ይህ ታሪክ የተጀመረው ፀጋዬ የታባለው ደራሲ ገፀ ባህሪ በጊዜው በነበረዉ በደርግና ሻዕብያ ፍልሚያ ማህበረሰቡን የማረጋጋት እና የማነሳሳት ስራ እንዲሰራ የጋዜጠኝነት ሙያዉ አስገድዶት ወደ አስመራ ለማምራት በጠዋት ተነስቶ ሮማንን ሲሰናበታት እና ስትሸኘዉ ነዉ። ሮማን ቆንጆ ነች ያያት ሁሉ ይማልላል። ፀጋዬን በጣም ነው የምትወደው ከተዋወቁበት ጊዜ ጀምሮ አስካሁን ሲጎጉለት የነበረው ተጋብተው አብረው መኖርን ነበር ለዛም በሁለቱም በኩል የሚጠበቅባቸውን እያደረጉ ከተጋቡ በኋላ ደስተኛ ኑሮ እንዲኖራቸዉ ቤታቸውን እያሟሉ ነበር ። ለዚህ ስራ ባይጠራ ኑሮ ለመሞሸር እና አብሮ ለመኖር ተቃርበው ነበር ። የተዋወቁት በአንድ ምሽት እርሱ እንደተለመደው የሴትን ቀልብ ለመሳብ ዘንጦ ወደ መጠጥ ቤት ሲሔድ ሮማንን ከሟች ወንድሟ ጋር ያገኛታል ወንድሟ ጋር ይተዋወቁም ስለነበር ፀጋዬን እንዲቀላቀላቸው ጋበዘው። በዛች ምሽት እስካዛሬ ያልታውየዉ የሮማን ውበት ቁልጭ ብሎ ታየው እስከዛሬ ምን ሁኜ ነው ይህ ቁንጅና ያልታየኝ ብሎ ራሱን ጠየቀ። አስደነሳት በደንብ ተግባቡ ቤት ቀየሩ በተደጋጋሚ መገናኜት ጀመሩ ተፋቀሩ አሁን ሊዳሩ ሁኔታዎችን እያመቻቹ ነው።በጊዜዉ የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ፀጋዬን በስራ ጠመደው ውሎ አዳሩ ስራ እና ስብሰባ ነው። ሮማንን ትቶ ወደ አስመራ አቀና።

አንድ ቀን የስራ ባልደረባው ከስብሰባ ሲወጡ እንዲዝናኑ ጋበዘው መጠጥ እየጠጡ እየተዝናኑ ፊያሜታ ጊላይ የተባለች ለየት ያለች መልአክት የምትመሰል ሴት ተዋወቁ የአስመራ ወንድ ሁሉ ስለ ፊያሜታ ነው የሚያወራዉ በቁንጅናዋ ምክንያት ዝነኛ ነች ሁሉም ያደንቃታል። ለአስመራ እንግዳ የሆነዉ ፀጋዬም በሷ ውበት ተማረከ ከተዋወቃት ቀን ጀምሮ ከሀሳቡ መጥፋት አልቻለችም በአጋጣሚም ለስራ ወደ ሌላ ሀገር ሔደው ፊያሜታን አገኛት። ለመጀመሪያ ጊዜ በነፃነት እጅ ለእጅ ተያይዘው ተዝናኑ እራት በሉ የምፅዋን ባህር እያዩ ተሳሳሙ አብረው አደሩ። ቀስ በቀስ በፍቅር ሰመጡ ፀጋዬ ሮማንን ረሳት ፊያሜታ የተለየች ሴት ነች ቀልቡንም ገዛችው። ፊያሜታ በጣም ብዙ ወንዶችን ታውቃለች በፍቅሯ ሲሰቃዩም ትደሰታለች ‹‹አንድ ወንድ ጋር መኖር በጣም ይሰለቸኛል››ትላለች። ፀጋዬን ግን አፈቀረችው።

‹ኦሮማይ› የተባለ ተቃዋሚ የውስጥ አዋቂ ፓርቲ አባል የሆኑ እና ፀጋዬን በስራው በጣም የሚጠሉት ባልደረቦቹ እርሱን በፊያሜታ በኩል ለማጥመድ ፀጋዬን አሳልፈሽ ስጭን ሲሏት እምቢ በማለት ምን ያክል እንዳፈቀረችው

እና ሙሉ ታሪኳን የሚገልፅ ኑዛዜን ያዘለ ደብዳቤ ፅፋለት ለእሱ ስትል እራሷን ለእነሱ አሳልፋ በመስጠት ትሞታለች። ፀጋዬ ልቡ በሀዘን ይሰበራል ከሚገባዉ በላይም ያዝናል። እጮኛዉ ሮማንም እሱን ለመጠየቅ አስመራ በሔደችበት ጊዜ ፀጋዬን እያፈቀረቻው ልቡ ግን ከፊያሜታ ጋር አብሮ ስለተቀበረ በጣም ታዝናለች እድሏን እያማረረች ቀለበቷን ወርውራለት ትሔዳለች። እሱም ያህችን ቆንጆ ነበልባል በልቡ ይዞ መቃብሯ ላይ እንደቆመ ታሪኩ ይደመደማል።

## 3.2. ደራሲው ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ

ሲራክ የተባለዉ ገፀ ባህሪ በሌሊት ብቻውን ከቤቱ ተቀምጦ ድርሰት እየፃፈ በተለያየ ሀሳብ ሲወጠር የስራ ባልደረባው የሆነችው ሰብለ በህሊናው እየመጣች ትታየዋለች።። ባለቤቱ ፅጌ በሲራክ የድርሰት ስራ በጣም ትናደዳለች። ሰው በሠላም በሚተኛበት በውድቅት ሌሊት እርሱ ብቻውን አፍጥጦ ሲጽፍ ስታየው ድርሰቱን አቁሞ የሠላም እንቅልፍ እንዲተኛም ትነግረዋለች። እኔን ከነመፈጠሬ እረስቶኝ ድርሰቱን ትዳር አድርጎ እየኖረ ነዉ ብላ ስለምታስብ ስራውን እንዲተው ትወተውተዋለች። የመኖሪያ ቤታቸው አዲስ አበባ ተረት ሰፈር ውስጥ ሲሆን አንድ ልጅ አላቸው። የተገናኙት እሱ በቤተሰብ ምክንያት ከድሮ ባለቤቱ ጋር ስላልተግባቡ በጣም እያፈቀራት ትታዉ ስለሔደች ብቸኝነቱን ለመርሳት አልፎ አልፎ ጎራ በሚልበት ፅጌ ደግሞ ገላዋን እና ውበቷን እየሸጠች በምትሰራበት መሸታ ቤት ሲሆን አግቢኝ የሚል ጥያቄ ስላቀረበላት እሷም በተደበላለቀ ስሜት በአንድ በኩል ከዛ ህይወቷ በመላቀቋ እየተደሰተች በሌላ በኩል ደግሞ እንዴት ያችን የመሰለች ሚስቱን እና ትዳሩን ትቶ እኔን ያገባኛል በሚል ስሜት ተዉጣ ትንሽ ካሰበች በኋላ ግን ሁሉን ነገር ትታ ወደ ትዳር ገቡ።

አሁን በህይወታቸው ብዙ ነገር አሳልፈዋል። በኑሯቸዉ ደስተኛ ስላልሆኑ ነጋ ጠባ ደህና ኑሮ መኖር አለብን ይህን ሰፈር ለቀን እንሂድ ለእኔ ለልጃችን ላንተም ጥሩ ሰፈር አይደለም ይህንን ድርሰትክን ተው የሚል ጭቅጭቅ ከቤታቸው አይጠፋም።ሲራክ የባለቤቱ ጭቅጭቅና የቤት አኪራዩ ቤቱን ልቀቁ ማለት ሰላሙን ነስተውታል ስራ ቦታ በስራው ደስተኛ አይደለም የድርሰት ስራውን እንዴት መቋጨት እንዳለበት እያሰበ በጣም ነው የሚያማርረው በዚህ ሁሉ ነገር ተወጣጥሯል። ይህንን ሁሉ ችግሩን ትንሽ የምታስረሳው እንዲሁም ድርሰቱን እያነበበች የምትገመግምለት በስራው እንዲቀጥልም የምታበረታታው ሰብለወርቅ ነች። ሰብለ የደስ ደስ ያላት ቆንጆ እና አስተዋይ ሴት ናት። ሁለቱን የሚያመሳስላቸው ነገር እሱም እሷም ልጅ አላቸው በኑሯቸዉና በትዳራቸውም ደስተኛ አይደሉም። የሰብለ ባለቤት ዘመነ ቁጡ ነዉ እየሰከረም በውሃ ቀጠነ ይነታረካታል ደስ ሲለውም ይመታታል። አንድ ቀን ሰብለ የሲራክን ድርሰት እያነበበች ባለቤቷ ሰክሮ ሲመጣ በር ለመክፈት ስትነሳ ድርሰቱን ስላገኘዉ በቅናት ተንጨርጭሮ ቀዶ ይጥለዋል። ያየችውን ማመን አቃታት እጅግ በጣም አዘነች ‹‹ምነው ድርሰቱን ባልተቀበልኩት›› ብላ ተፀፀተች። ለሲራክ ስትነግረው ግልባጭ ስለሌለው በጣም ቢደነግጥም እንደገና በንፁህ መንፈስ ለመጀመር እድል ይገኛል ብሎ አፅናናት በዛዉ ስለትዳሯም አጫወተችው በጣም አዘነላት ወደዳትም እሷም ወደደችው ድብቅ የፍቅር ግንኙነት ጀመሩ። ፍቅር ውስጥ ሰምጠው ከሲራክ

ቤት በድብቅ ይገናኛሉ የማያውቁት ደስታ ተሰምቷቸዋል፡፡ ሲራክ መፅሀፉን እንዴት መቋጨት እንዳለበት ከብዶት የነበረው ሀሳብ ለቆት እንደዉም በአዲስ መንፈስ እንደገና ለመፃፍ ተነሳሳ፡፡

ፅጌ ከጎረቤቷ እትዬ አልታዬ ጋር በመሆን ድርሰቱን ለማስቆምና ባሏ ለምን እንደተቀየረ ለማወቅ ማጣራት ጀመረች ከሰብለ ጋር ድብቅ የፍቅር ግንኙነት እንዳላቸው ደረሰችበት፡፡ ሲራክ የፅጌ እና የሰብለ ነገር እንደማይሆን ስላወቀ የሰብለ ባለቤት ጋር በመሔድ ‹‹አንተ ስለማትረዳት ነው እንደዚህ አይነት ስህተት የሰራችው ልትረዳት ይገባል›› ብሎ ያናግረዋል ዘመነ በጣም ተናዶ ይደበድበዋል፡፡ በመጨረሻ ግን በሲራክ ሁኔታ ተገርሞ ይፀፀታል ሚስቱን እንደበደላትም ተረድቶ ባልጠበቀቸው ሁኔታ ይቅርታ ጠየቃት ሰብለም በባለቤቷ መለወጥ ተደስታ ይቅርታ አረገችለት፡፡ ፅጌ የራሷን ሁኔታ በማዳመጥ እና ከውትድርና የተመለሰ ጎረቤታቸው ሊጠይቃት በሔደ ጊዜ የመከራትን ምክር ልቧ ውስጥ በማስገባት እራሷን ቀይራ ከሲራክ ጋር ተቀምጠዉ በመነጋገር ችግራቸዉን ፈቱ፡፡ ሲራክ የጀመረውን ድርሰት ሚስቱ ፈቅዳለት እያገዘችው፤ የመፃፍ ፍላጎቱ ጨምሮ ደስ እያለው ይፅፋል፡፡ ህወታቸውንም በደስታ መኖርና መምራት ይጀምራሉ፡፡

## 3.3. ከአድማስ ባሻገር ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ

ታሪኩ የሚጀምረው ዋና ገፀ ባህሪው አበራ ብቻውን በሀሳብ ባህር እየዋኜ ማንነቱን ሲፈትሽ ከዛም ሱዛን ሮዝ የተባለች የድሮ ፍቅረኛውን ሲያስታውስ ነው፡፡ ታሪኩ በዋናነት የሚያጠነጥነው በአበራ እና በዙሪያ ባሉ ገፀ ባህሪዎች ላይ ነው፡፡ አበራ በስራውና በህይወቱ ደስተኛ አይደለም ህልሙን እየኖረው አይደለም፡፡ ሀይለማርያም የተባለ የልብ ጓደኛ አለው እሱም ቢሆን በስራዉ ደስተኛ አይደለም፡፡ ከልጅነት ጀምሮ አብረው ተምረዋል ሁለቱም የጥበብ አድናቂዎች ናቸው፡፡አበራ በውስጡ የታመቀ የመሳል ጥበብ አለው ሀይለማርያም መፅሀፍ ከእጁ አይለይም ሁሌም ያነባል ድርሰት ይደርሳል፡፡ ሁለቱም ሲጋራ ያጨሳሉ መጠጥ ይጠጣሉ ተመሳሳይ የህይወት ጥሪ አላቸው፡፡

ሉሊት የአበራ ፍቅረኛ ነች የተዋወቁት ለፋሲካ ዋዜማ ሆቴል ቤት ተያይተው አብረው ዳንሰው ነው፡፡ ወንድን ማንበርከክ እና ከእግሯ ስር ማሰገድ ልዩ ስሜት ይሰጣታል፡፡ ‹‹ማንም ወንድ እኔን ትቶ አይሔድም›› ትላለች፡፡ ካልሰገዱላት ሰውነቷ አይታዘዝላትም፡፡ይህ ፀባይዋ እልህ ያስያዘዉ አበራ ስለሷ ማሰቡን ሊያቆም አልቻለም፡፡ ከተዋወቁ በኋላ መገናኜት ጀመሩ ከዚያም ስሜታቸዉ ወደ ፍቅር ተቀይሮ አብረው አደሩ በነጋታውም እንዲያገባት ጥያቄ አቀረበችለት፡፡ እሱም ለመወሰን ከበደዉ በህይወቱ ደስተኛ አይደለም ለራሱ ህይወቱን እንዴት መሙላት እንዳለበት ሳያውቅ እንዴት ወደ ትዳር መግባት እችላለው ብሎ ጠየቀ በአንድ በኩል ደግሞ የወንድሙ ጋሽ አባተ ነጋ ጠባ ‹‹አግባ የእኛ ዘር የሚቀጥለው ባንተ ብቻ ነው እኔ መውለድ አልችልም የራሴን ህይወት ትቸ ያስተማርኩህ እንደዚህ አጉል እንድትሆን አይደለም›› የሚለው ምክሩ ትዝ አለው ለማግባትም ወሰነ፡፡ እናቱና የወንዱሙ ሚስትም በጋብቻዉ ደስተኛ ሆኑ፡፡ በሀይለማርያም እና በሉሊት እርዳታ ስራውን ለቆ

የውስጡን ስሜት በማዳመጥ ስዕሉን ለመሳል ዝግጅት ላይ ነው። አንድ ቀን ግን በህይወቱ ያልጠበቀው መጥፎ አጋጣሚ ተፈጠረ በተሳሳተ መረጃ ተነስቶ ሚስቱን ሉሊት የማገጠችበት ስለመሰለዉ በስህተት ሰው የመግደል ሙከራ በማድረጉ እስር ቤት ገባ ። በዚህ የተበሳጩት እናቱ ህወታቸው አለፈች ። ጋሽ አባተ ሀይለማርያምን ከሉሊት ጋር ስላገኘው በደም ፍላት ‹‹ቅንተ ነህ ለዚህ ሁሉ ያበቃከው››ብሎ እሱን ገሎ እራሱን ያጠፋል። ይህ ሁሉ አልፎ ፍርድ ቤት ሁሉንም አጣርቶ ሶስት ዓመት እስራት ይፈርድበታል ሉሊትም ሁሉን ትታ ይቅር ብላው እንደገና ለመኖር ሲያንሰላስል ታሪኩ ያልቃል።

## 3.4. የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና

### 3.4.1.ኦሮማይ የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና

**ሮማን**

**አካላዊ አሳሳል**

ቆንጆ ከንፈሯ ውብ ጥርሷ ትኩስ የተፈለቀቀ ለጋ የመስኖ በቅሎ እሸት የሚመስል አፈር የሚነካው ገላ ያላት አትመስልም፤ እግዚአብሔር እጁን ታጥቦ ያለ የሌለ ጥበቡን ያፈሰሰበት ገላ ነው ያላት ጡቶቿ የተወጠሩ የማለዳ ፀሀይ የሚመስሉ ጉንጮቿ ሙሉ ጨረቃ የሚመስለው ክብ ፊቷ ላይ ከንበል ደፋ ያለው ረጅም ጥቁር ፀጉሯን ሲይዋት እነደ ጥኡም ሙዜቃ ደስ የሚል።

**ማህበራዊአሳሳል**

የዋና ገፀ ባህሪው ፀጋዬ እጮኛ ነች በጣም ታፈቅረዋለች እሱም እንደዛዉ።በጣም ቆንጆ ስለሆነች የሴቶችንም ቀልብ ሳይቀር ትስባለች።ሴቶች በአይናቸው እንደ ሽንኩርት ላጥ ያደርጓታል። ‹‹ቅድሌ ሆኖ ሴቶች አይወዱኝም ባዩኝ ቁጥር ይቀኑብኛል እኔም አልወዳቸውም ያለ ሴት ጠላት የለኝም ምናምናቸውን ያቀምሱኛል››ትላለች ። በሀይማኖቷ አክራሪ ጴንጤ ስትሆን መፅሀፍ ቅዱስ ይዛ የምትንቀሳቀስ ወሬዋ ሁሉ ‹‹ የእግዚአብሔርን ቃል እንስማ ›› ነበር ሆኖም አብረዋት የሚውሉ የሀይማኖት ጓደኞቿ ነገርየውን ወደ ፖለቲካ ስለቀየሩት እና አላማቸውም እሱ እንደሆነ ስላወቀች ወደ ኦርቶዶክስነት ተቀይራለች። የኑሮ ደረጃዋ መካከለኛ የሚባል ነዉ።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

ሮማን አኩራፊ አፍቃሪ ቅናተኛ እና ራሷን የምትወድ ስስ ልብ ያላት አስተዋይ ስለወደፊት አርቃ የምታስብ ራሷን የምትጠብቅ በነገሮች ስትናደድና ደስ ያላላት ነገር ሲኖር ተናጋሪ ነች። ነገር በሆዷ መያዝ አትችልም የደነደነ ልብ የላትም አልቃሻ እና ናፋቂ ነች ለፍቅሯ ታማኝ ነች ታሪኩ እስኪያልቅ ድረስ እጮኛዋ ፀጋዬን በታማኝነት ስትጠብቀው ይታያል። በመጨረሻ ግን እሱ ስለከዳት እና ልቡ እዚም እዛም የሚል ወንድ ስለማትወድ ሌላ ሴት ስላፈቀረ እየወደደችው ትታው ሄዳለች። ‹‹የምወዳቸው ወንዶች ለምን እንደሚከዱኝ አላውቅም አግኝቸ ማጣት የአርባ ቀን ዕድሌ ነው መሰለኝ››ትላለች።

ከዚህ ቃል ተውኔት የምንረዳው አፍቃሪ እንደሆነች እና በተቃራኒው ወንዶች ልቧን እንደሚሰብሩት እናም በጣም እንደምታዝን ነዉ።

ሮማን ቡና ማፍላትን ወደ ኪነታዊ ፈጠራ ከፍ ታደገዋለች። የምታፈላው ለሱስ አልያም ለአምልኮ አይደለም ለኪነታዊ ውበቱ ስትል ነው። ቡና ስታፈላ ‹‹ቡና ማፍላት ረጋ ብሎ ነው ስርዓቱ ውበቱ ነው›› ስለምትል ተጣጥባ በሀገር ባህል ልብስ ተውባ ነጠላዋን ተከናንባ ቡናው ታጥቦ ተጠጥቶ እስከሚጨረስ በልዩ መልክ ተመስጣ በጥንቃቄ ነው በዚህ የአፈላል ጥበቧም ትኮራለች።

**ሞራላዊ አሳሳል**

ይች ገፀ ባህሪ የምር የሴት አንጀት እና ጥሩ ስብዕና ያላት አሳዛኝ ነች። ከልቧ ታፈቅራለች ለቆመችለት አላማ እስከመጨረሻው የምትሄድ ድል ማድረግን የምትፈልግ ሽንፈትን የማትወድ ባሏ ሌላ ሴት እንደደረበባት ባወቀች ጊዜ እያፈቀረችው ለእርሷ ቦታ የሌለው ልብ አቅፋ ከመኖር ለብቻዋ መሰቃየትን የመረጠች ትልቅ ውሳኔ የምትወስን ቆራጥ ሴት ነች።

**ፊያሜታ ጊላይ**

**አካላዊ አሳሳል**

ፊያሜታ ቆንጆ ጥርሶቿ ታይተው የማይጠገቡ ሁሌም ከእጇ መፋቂያ አይጠፋም ከጥርሷ አይለይም ጥርስ አፋፋቅም ኪነታዊ ነው የውበት አምላክ በጥንቃቄ የደረደራቸው የባህር ዕንቁዎች ይመስላሉ። ሰሜናዊቷ አበባ ፈገግታዋ እንደ ጠፍ ጨረቃ ይናፈቃል ቁመናዋ የባህር ዳር ቄጠማ የመሰለ ለግላጋ ነው አስደማሚ ውበት አላት። ከንፈሯ የልብ ቅርፅ ያለው ጥርሶቿ በረዶ መሳይ ሸንጧ እጥፍ ዝርግት የሚል የሰውን ቀልብ የምትስብ መዘነጥ መዋብ መሽቀርቀር የምትወድ ውድ ባልሆኑ እና ቀለል ባሉ ጌጦች በቀላሉ የምታጌጥ የመዋብ ችሎታ ያላት መኳኳል የማታበዛ ወጣት ናት። ፀጋዬ ውበቷን እንዲህ ሲል ይገልፀዋል።‹‹ባህሩ የቆመችበትን ድንጋይ ይለዉ ይመስላል። ከባህር የሚወጣው ቀዝቃዛ አየር ጠጉሯን እያነሳል አየር ላይ ይነሰንሰዉ ነበር።

በቀጭን መያዣ ክብ ትከሻዋ ላይ ተንጠልጥሎ ጀርባዋን ገልጦ የሚያሳይ ነጭ አጥር ያለ የበጋ ቀሚስ ለብሳለች የባህር አምላክ የምታመልክ ነጭ እርግብ ትመስላለች፡፡ ›› (1975፡200)

**<u>ስነልቦናዊአሳሳል</u>**

ፊያሜታ ከልጅነቷ ጀምሮ እንደ ስሟ ትንሽ ነበልባል እንደሆነች በራሷ አንደበት እንዲህ እያለች ትናገራለች ‹‹በህፃንነቴ እሳት ነበርኩ እያለቀስኩ እቃ እየሰበርኩ ከቤት እየጠፋሁ እናት እና አባቴን ሳስቸግራቸው ነበር፡፡ ብቻየን መተኛት ደግሞ አልወድም ነበር ብቻየን ካስተኙኝ ሌሊቱን በሙሉ ሳለቅስ አድራለው ከነሱም ጋር ተኝቼ ሲጫወቱ የሰማሁ እንደሆነ አለቅሳለሁ፡፡›› (1975፡92) ይህ ቃለተውኔት እንደሚያስረዳው ሀይለኛ እንደነበች እና በዚህም ምክንያት ፊያሜታ ጊሊያ (ትንሽ ነበልባል) እንደተባለች ነው፡፡ ካደገች በኋላ ለየት ያለ ስብዕና ያላት ትልቅ ነበልባል በራሷ የምትተማመን ወንድን ልጅ በማማለል በፍቅሯ ማንበርከክ እና በእሷ ፍቅር ሲሰቃዩ ማየት የምትወድ በተለይ ደግሞ ባለትዳር ወንድ በጣም የምትወድ ሴት ነች፡፡ በህይወቷ ብዙ አይነት ወንዶች ጋር ግንኙነት ነበራት ሁሉንም ለጊዜያዊ ደስታ ነበር የምትፈልጋቸው ለሴት ልጅ ያላቸው ግምት በጣም ስለሚያናዳት ሁሌም ገንዘባቸውን በልታ በፍቅሯ አስክራ ህይወታቸው ሲዘበራረቅ ማየት ያስደስታታል፡፡‹‹አንድ ወንድ ጋር ብዙ ጊዜ መቆየት አልችልም ሳየው ጥለሸው ብረሪ ብረሪ ይለኛል››ትላለች፡፡ ይህን የምታደርገው ግን ክፉ ስለሆነች አይደለም በህይወቷ የሚመጡ ወንዶች የማትፈልጋቸው አይነት ስለሆኑ እና በሴት ግፍ ስለሚሰሩ ለመበቀል ነው፡፡ ልቧ ፍቅር የሚያውቅ ነው ለማለት የሚያስችለን ጉዳይ በፀጋዬ ፍቅር ማንነቷ ተቀይሮ ለሱ ስትል እጅግ የምትሳሳለትን ህይወቷን አሳልፋ የሰጠች ሴት በመሆኗ ነው፡፡ በእልክ የተሞላች ቅናተኛም ነች፡፡ እንደ ልማድ ሆኖ በወሬዋ መሃል ውሸት አይጠፋም ይህንን የሚያረጋግጥልን ቃለተውኔት ‹‹ፊያሜታ ጊላይ አንድ ጠባይ አላት እውነት እና ውሸት ደባልቃ ነው የምትናገረው፡፡ ትንሽ እውነት ይዛ ውሸት ትጨምርበታለች እና ከምትናገረው ውስጥ የትኛው እውነት የትኛው ውሸት መሆኑን ለይቶ ለማወቅ ያስቸግራል ታዲያ እንዲህ የምታደርገው አመል ሆኖባት እንጂ ክፋት አይደለም፡፡››(1975፡261)

**<u>ሞራላዊ አሳሳል</u>**

ፊያሜታ የምታውቃቸው ወንዶች ሲያዋርዷት ዝቅ ዝቅ ሲያደርጎት በተቃራኒው ደግሞ ፀጋዬ ሲያደንቃት እና የተለያየ ደስታን ሲሰጣት እናያለን፡፡ በአሸናፊነት የተሞላች ትሁት እንደሆነችም መረዳት እንችላለን ተግባቢ ስትሆን አንደበቷ ይጣፍጣል፡፡ በታሪኩ ትልቅ ሚናን የተጫወተች አነጋጋሪ ገጸ ባህሪ ነች ለራሷ ከፍ ያለ ግምት ያላትና በአቋሟ የምትፀና ሴት ነች፡፡

**<u>ማህበራዊ አሳሳል</u>**

ይህች ገፀ ባህሪ አስመራ ተወልዳ ያደገች ሲሆን ትዳሯ ስላልተመቻት ፈትታ ከቤተሰቦቿ ጋር ነው የምትኖረዉ ፡፡ደመወዟ አነስተኛ ቢሆንም ስራ አላት፡፡ በወንዶች ዘንድ ተወዳጅ ነች ነገርግን የተወሰኑ ወንዶች አጭበርባሪ

ነች በወንድ አትጸናም የሚል ስም አውጥተውላታል ስለሚፈሯት አይቀርቧትም። ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ ወጣ ብላ የራሷን ኑሮ ትኖራለች።

## 3.4.2. ደራሲው የሴት ገፀ ባህሪያት አሳሳል ትንተና

### ፅጌ

#### አካላዊ አሳሳል

ፅጌ ጠይም አሣ መሣይ ቆንጆ ዝንፍልፍል እያለ የሚወርደው ጥቁር ሉጫ ፀጉሯ ላይ ሁሌም ሻሽ ሸብ አርጋት ታስራለች ግን ሻሹ አይረጋም  አይኖቿ ትላልቅና ቦግ ቦግ ያሉ ናቸው  ደረቷ ትኩስ የተላጠ ሽንኩርት ይመስላል ፈገግ ስትል ሀሞት የሚመስለው ንቅሳት ወተት ከሚመስሉት ጥርሶቿ ጋር እየተነፃፀረ ልብ ይማርካል።

#### ማህበራዊ አሳሳል

ይች ገፀ ባህሪ የበፊት ስራዋ ሴተኛ አዳሪነት ቢሆንም አሁን ሲራክን አግብታ የቤት እመቤት ሆናለች። በማህበራዊ ህይወቷ ደካማ ነች ከምትኖርበት ተረት ሠፈር ከእትዬ አልታዬ በስተቀር ምንም አይነት ወዳጅም ሆነ ቤተሰብ የላትም። ቀብር፣ ስብሰባ፣ ዕቁብ የሚባል ማህበራዊ ኑሮ አያስደስታትም ከቤትም ቡናዋን አፍልታ ቤቷን ደመቅመቅ አድርጋ መቀመጥ ያስደስታታል እትየ አልታዬም ቡና ሲፈላ እየመጡ ያጫውቷታል ያማክሯታል። አንድ ልጅ አላት ከዘመድና ቤተሰብ ጋር ቀረቤታ የላትም ቤተሰቧ ትዳሯ እና ልጇ ናቸው ። ከሰው የተገለለች ናት። በእምነቷ ክርስቲያን ብትሆንም በጠንቋይና በባዕድ ነገር የምታምን መሆኗን የሚያረጋግጥልን ቃለተውኔት ‹‹ስንት ቃልቻ ሰግጀ ለስንቱ ታቦት ተስየ ያገኘሁትን ልጄን ለቀቅ››(1972፡44)

ኢትዮጵያዊ ባህሏንም በተወሰነ ትጠብቃለች እንደ አብዛኛው ሚስት የቤት እመቤት በመሆኗ ባሏ ሲመጣ ቤቷን ታሟሙቃለች በጠዋት ተነስታ ቁርስ አብልታ ትሸኘዋለች። ልጇንም በሚገባ ትንከባከባለች። የኑሮ ደረጃዋ ዝቅተኛ በመሆኑ ምክንያትም ደስተኛ አይደለችም ። ባሏ ሳይመጣ እህል በአፍዋ አይዞርም እርሱን ጠብቃ አብራ ነው የምትበላዉ። ‹‹እኔ እንደ ሴቱ ብቻየን መብላት አልወድም ከጉሮሮየም አይወርድም›› ትላለች።

#### ስነ ልቦናዊ አሳሳል

የዋህ አፍቃሪ ብትሆንም በኑሮዋ ደስተኛ ስላልሆነች ነጋ ጠባ ትነጫነጨለች ባሏን በንትርክ ያሰለቸችም ነች። ‹‹ግን አሁን ተለውጠሻል ደግነት ፍቅርና ታማኝነት አንሶሽ ሳይሆን የምወደዉን ሰላም ትነፍጊኛለሽ››

(1972፡199)

ይህ የባሏ ሲራክ ቃል ተውኔት የሚያሳየው ቅንነትና አፍቃሪነት ሳያንሳት የባሏን ስራ ስለማትወደው የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ ስለሆነ እና ሌላ ሰፈር ሔዳ የተሻለ ኑሮ መኖር ስለምትፈልግ ባሏን ነጋ ጠባ የምትጨቀጭቅ እና የምትነጫነጭ ሴት እንደሆነች ነዉ፡፡መማርን ያን ያህል አታበረታታም ‹‹መማር ምን ይጠቅማል›› ትላለች፡፡ ‹‹ጤና የለኝም አሞኛል››ማለትም ታዘወትራለች፡፡

**<u>ሞራላዊ አሳሳል</u>**

የተከበረች ባለትዳር ስትሆን እራሷ እንደምትወድም የድሮ ታሪኳ ላይ ሴተኛ አዳሪነት የመረጠችው ሰው ቤት ታንቃና ሌባ እየተባለች መኖር ስለማትፈልግ ነው፡፡ የተመቻቸ ኑሮ ትመርጣለች፡፡የቤቷን ሰላም በጭቅጭቅ አደብዝዛዋለች ባሏም የሚገባትን ክብር አይሰጣትም እሷ እያለች ሌላ ሴት አፍቅሮ ደርቦባታል፡፡ በመጨረሻ ግን በሱ ሀሳብ ተስማምታ ትሁት ስትሆን ይታያል፡፡ ትንሽ ጉራ ቢጤ አለባት ድል ማድረግን ትፈልጋለች ለህልሟ ትተጋለች፡፡

**<u>ሰብለወርቅ</u>**

**<u>አካለዊ አሳሳል</u>**

ሰብለ ቆንጆ ከንፈሯ ወፍራም ስታዝንና ስትደሰት የታችኛው ወፍራም ከንፈሯን ጣል የምታደርግ አፏ ሰፋ ብሎ ጥርሶቿ በጥንቃቄ የተደረደሩ ትናንሽ እንቁዎች የሚመስሉ ፀጉሯ አጭር በአብዛኛው ከግንባርዋ ላይ ከንበል ደፋ የሚል ፊቷም ሰፋ ያለ ክብና ሙሉ ጨረቃ የሚመስል ፈገግታ የተላበሰ ውበትቷ የሚያጓጓ ጡቶቿ የበሰለ የበርሃ ሎሚ የሚመስሉ ሰውነቷ ለግላጋ አለባበሷ ዘናጭ ነች፡፡

**<u>ማህበራዊ አሳሳል</u>**

ሰብለ የምትወደድ እናቷን በልጅነቷ ያጣች የዋና ገፀ ባህሪው ሲራክ የስራ ባልደረባ ነች ፡፡ ባለ ትዳር የልጆች እናትም ነቾ፡፡ ከሲራክ ጋር ድብቅ የሆነ የፍቅር ግንኙነት ጀምራ የነበረች በሷና በባሏ ፍቅር ደስተኛ ያልሆነች ታታሪ ሰራተኛ ጥበብን የምታደንቅና ሀብታም ነገር ግን ሀብቷ በባሏ ውርስ የተገኘ በመሆኑ እና ባሏ ስለገንዘብ ብቻ ስለ ሚጨነቅ ሰለ ሀብት ግድ የሌላት ከሰው ጋር ያን ያህል የገነነ ቅርርብ የሌላት ጓደኛ የማታበዛ ሴት ነች ፡፡ የሰብለ የኑሮ ደረጃ ጥሩ የሚባል ጤናማ ልጆች ባል ቤት መኪና ጥሩ ደመወዝና ጥሩ ስራ አላት፡፡

**<u>ስነ ልቦናዊ አሳሳል</u>**

ሰብለ ወርቅ ልቧ ለፍቅር ቦታ የሌለው ነው፡፡ ልቧ የተቆለፈው ገና በልጅነቷ ጀምሮ ነው እናቷን በጣም አጥብቃ ትወድ ነበር የትም ስትሔድ ፈፅሞ አትለይም ነበር እናቷም የርሷ ነገር ጭንቀታቸው ነበር ነገርግን በድንገተኛ

ሞት ሰብለን ትተዋት ሔዱ። ከእናቷ ሞት በኋላ ፍቅር እንደ ፍም እየፈጃት በልቧ ተዳፍኖ ቀረ። ሌላ ሰው የማፍቀር ፍርሃት አደረባት ከምትወደው ሰው ጋር መለየትን ስለምትፈራ ማንንም በሙሉ ልቧ መውደድ እነዳትችል አደረጋት ይህ አይነት ውሳኔ በልጅነቷ ከደረሰባት የእናት ፍቅር ድንገተኛ መለየት የመነጨ መሆኑ በምልሰት ተተርኳል። ስለገንዘብ ግድ የላትም በባሏ ስካርና ስድብ የተሰላቸች የሱ ብር ብር ማለት ያማረራት እና ከባልዋ ፍቅር የምትፈልግ ግን በተቃራኒው ንቀትና ስድብ የሚሰጣት ትዳሯን መፍታት ብትፈልግም ድፍረት የሌላት ችግሮች ፈሪ ያረጓት ለልጆቿ ስትል ሁሉን ችላ የምትኖር ህይወት ፍትህ ያኳላታል ብላ የምታስብ ሴት ነች ለዚህ ደግሞ ተከታዩ ቃለ ተውኔት ማስረጃ ሊሆነን ይችላል

የሌሎችን ድፍረት "ድለው ምነው እንደነሱ ድፍረት በሰጠኝ እያልኩ ከማድነቅ ሌላ የራሴን ህይወት መኖር አልችልም የራሴን ትች የሌሎች ህይወት ውስጥ ነው የምኖረው ይግረምህና ለዚህ ነው ልብ ወለድ መፅሀፍ ማንበብ የምወደው"(1972፡17)

እዚህ ላይ እንዳለችዉ ልብወለድ ማንበብ የምትወደው እርሷ ለማድረግ የማትደፍረውን ልብወለድ ላይ ያሉ ገፀ ባህሪያት ሲደፍሩላትና ሀሳቧን ሲገልፁላት በነሱ ውስጥ ራሷን እየሳለች ስለምትደሰት ነው።

**ግብረገባዊ አሳሳል**

ሰብለ በትህትና የተሞላች ሰው የምታከብር ስነ-ሥርዓት ያላት በሰዎችም ዘንድ ተወዳጅ ገፀ ባህሪ ናት።

**ውባንች**

**አካላዊ አሳሳል**

ስትናገር ትንሽ እንቅርቷ ከፍ ዝቅ እያለ አንገቷ ላይ ይጫወታል ቀይ ስለሆነች እንቅርታም አንገቷ ላያ ያለዉ ንቅሳት ቦግ ብሎ ይታያል አይኖቿ ያማምራሉ።

**ማህበራዊአሳሳል**

ወሎየዋ ውባንች ታታሪ የቤት ሰራተኛ ነች። በ1977 ዓ/ም በድርቅ ምክንያት ቤተሰቦቿ በማጣቷ ተወልዳ ያደገችበትን ሀገር ትታ ወደ አዲስ አበባ ተሰዳለች። ነገርግን የገጠሩ ባህሏን አረሳችም አነጋገሯ አስተሳሰቧ አልተበረዘም። ፈጣሪዋን የምትፈራ የዋህ ሴት ነች። ትምህርት ስላልተማረች አሰሪዋ ሲራክ እንድትማር አድርጓታል ነቃ ያለች ጎበዝ ተማሪ ነች።

**ስነ ልቦናዊ አሳሳል**

በድርቅ ምክንያት ልጇን ባሏ ቤተሰቦቿን ስላጣች ቶሎ ሆድ የሚብሳት ሩህሩህ ነች። እህል ወድቆ ካየች እንባ

ይተናነቃታል ታለቅሳለች ግፍ ነዉ ፈጣሪ ያያል ዘመዶቼ ይህን አጥተው ነው አይኔ እያየ በርሃብ ያለቁብኝ ብላ የድሮ የሀገር ቤት ትዝታዋ ይታወሳታል፡፡ በፊት ከሀገሯ ሳትወጣ ጥሩ ኑሮ እንደነበራት የሚያሳየን (1972፡47) ላይ ውባንች በሀሳብ ጭልጥ ብላ ስታስታውስ የሚያብራራዉ

‹‹ ከሞቀ ጎጆዋ ውስጥ ጭስ ቡልቅ ቡልቅ ሲል ጎመኑ ሲንተከተክ

እሷ ልጆቿን ይዛ በአንቀልባ አዝላ ጎንበስ ቀና ስትል ጥገቶቿም

እንቧ እያሉ ሜዳውን አቋርጠው ሲመጡ ጥጃዎቿ እንቧ ሲሉ

ደሮዎቿም ሲሰፍሩ የባሏ ማሳ የጓሮ አትክልት ጎመኑ ቃሪያው

ሽንኩርቱ የጠጅ ሳሩ ጤናአዳሙ ውሃ የምትቀዳበት ምንጭ

እንጨት የምትሰብርበት ጫካ ሜዳ ሽንተረሩ ፊቷ መጥቶ ድቅን

አለ››

እናም ይህን ሁሉ ነገር ያሳጣትን ድርቅ አምርራ ትጠላዋለች እህል በጣም ታከብራለች፡፡ ድርቅ እህል ማጣት ስለሚያሳስባት ከንግግሯ ውስጥ ድርቅ እና ማጣት አይጠፋም፡፡

**<u>ሞራላዊ አሳሳል</u>**

ትሁት አሰሪዎቿን የምታከብር ፈጣሪዋን የምትፈራ በዘማናዊነት ያልተበረዘ ንፁህ ማንነት ያላት ሰው የማትንቅ ሁሉንም አክባሪ ተወዳጅ ገፀ ባህሪ ነች፡፡ እሷ ግን የቤት ሰራተኛ ስለሆነች የክብር ደረጃዋ የወረደ ነው፡፡

**<u>እትዬ አልታዬ</u>**

**<u>አካላዊ አሳሳል</u>**

ረጅም ቁመናቸው የሚያምር ወገባቸው ቀጭን አሮጊት ፀጉራቸው ሽበት የወረሰው ችምችም ያለ ጎፈሬ ሲያወሩ ወርቅ ጥርሳቸው ብልጭ ብለጭ የሚል ረጅም ቀሚስ ለብሰዉ ወገባቸው ላይ መቀነት ሽብ የሚያረጉ፡፡

**<u>ማህበራዊ አሳሳል</u>**

ለብዙ ዘመን የታወቁ ቃልቻ ቡና ካዳሚ ነበሩ፡፡ የሚኖሩት በየቤቱ እየዞሩ የቡና ሲኒ አይተው በመጠንቆልና በመቀላወጥ ነው፡፡በዚህ የተነሳ ወሬያቸው እምነታቸው ሁሉ ቃልቻ ካራማ አድባር ነዉ ሌላ ስራ የላቸውም ፡፡ለዚህም እንደ ምሳሌ ‹‹ታሪክ ነዉ ቡና ከሀገር ጠፋ አድባሯን ሊያጣሉን ካርማዋን ሊያሸሹብን የቡናዉ ሺሂ

ዘንግ ደጉን ቀን አምጣልን አዎን። ጀበናን ማስደንገጥ ደግ አይደለም የጥቁር ጀበና አምላክ ምሱን ካላገኜ ጋኔሉም አዉላዉን ካላሸተተ አድባሯ ትጣላለች።ቈ(1972፡44) እትዬ አልታዬ ምንም ዘመድ፣ባል እና ልጅ የሌላቸው መካን ናቸው።

**<u>ስነ ልቦናዊ አሳሳል</u>**

ሁሉ ነገራቸው በቡና የተሰራ ይመስል ጀሯቸው ቡና የሚወቀጥበትን ቤት  ሲያዳምጥ ነው የሚውለው። ቡና ተወግጦ ተጥዶ የሚያፈላበትን ደቂቃ አይስቱም ስኒያቸው ይዘው ልክ በስዓታቸው ከተፍ ይላሉ። ስለ ማግባትና ልጅ ስለመውለድ ይህን ያክል ገድ አልነበራቸውም አንድ ቀን ግን እርግብ እቤታቸው እንቁላል ፈልፍላ ልጆቿን ስታበላ አይተው ልባቸው ተነካ አምርረው አለቀሱ አለመውለዳቸው ያለዘር መቅረታቸውና ከሞቱ በኋላ ምንም ስም እንደሌላቸው ምንም እንደማይቀራቸው አስበው እንባቸውን አዘሩ በዚህም ምክንያት ልባቸዉ የተነካ ብቸኛ አሮጊት ናቸው።

**<u>ሞራላዊ አሳሳል</u>**

እድሜቸው የገፋና ለዛ ያላቸው ቀልድ አዋቂ ስለሆኑ በሰው ዘንድ ተደናቂ ናቸው ሰዎችም ያከብሯቸዋል። በሀይማኖታቸው የፀኑ ባይሆኑም ለሰው ግን ክፉ የሚያስቡ እና ጨካኝ አይደሉም። ባእድ ነገር በማምለካቸው ጥሩ አስተሳሰብ አላቸው ለማለት ቢያዳግትም ለሰው አሳቢ ስለሆኑ የራሳቸውን ኑሮ ስለሚኖሩና ግልፅ ስለሆኑ ሰዋዊ  ስብዕናቸው ጥሩ የሚባል ነው።

**<u>ማርታ</u>**

**<u>አካላዊ አሳሳል</u>**

በዝርዝር ስለውጫዊ ውበቷ የተቀመጠ ነገር ባኖርም ቆንጆ የማርያምን ስዕል የምትመስል የብዙ ወንዶች ልብ ማንበርከክ የምትችል ማራኪ የደስ ደስ ያላት ገፀ ባህሪ ነች።ውብ አለባበሷ እንደሚማርክ ተገልፆል።

**<u>ማህባራዊአሳሳል</u>**

የሲራክ የመጀመሪያ ሚስቱ ነች ልጅ ወልደዋል የሚኒስቴር ልጅ ነች በቤተሰቦቿ ተከባ በእንክካቤና በፍቅር ያደገች ከማህበረሰቡ ጋር ጥሩ መስተጋብር ያላት በሰው ዘንድ ተወዳጅ በሀብት ተቅበጥብጣ የምትኖር የተማረች እና ሰው የማትንቅ ተግባቢ ቤተሰቦቿን የምታከበር ለእነሱ ስትል ሒይወቷን የምትሰዋ በእነሱ ምክንያትም የምታፈቅረዉ ባሏን ጥላ ልጆቿን ይዛ ከቤተሰቦቿ ጋር የምትኖር በመጨረሻ ጭካኔዋን ያሳየች ገፀ ባህሪ ነች።

**<u>ስነልቦናዊ አሳሳል</u>**

በኑሮዋ ደስተኛ የነበረች ጥበብን ስለምታደንቅ በአጋጣሚ የተዋወቀቻው ደራሲ ጋር ቀስ በቀስ በፍቅሩ የምትወድቅ እርሱን አግብታ ድርሰት እያነበበች ከእርሱ ጋር የመኖር ህልሟ ተሳክቶ በፍቅር ከእርሱ ጋር ለመኖር ብትጀምርም ቤተሰቦቿንና በጊዜው በነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋት ደስታዋን እና ትዳሯን ያጣች ፍላጎቷን ጠግባ ያልኖረች አስተዋይ ነገር ግን ራስ ወዳድ ገፀ ባህሪ ነች፡፡

**<u>ሞራላዊ አሳሳል</u>**

የሚኒስቴር ልጅ ስለነበረች በጊዜው በሰው ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣት ግን በስልጣን እና በዝና የማትኮራ እና ሰው የሚያደንቃት ፍላጎቷን በቤተሰቦቿ የተነሳ የተነጠቀች በሥነ-ሥርዓት ተቀጥታ ያደገች ታለቅነትና አሸናፊነትን ብቻ የምታውቅ ገጸ ባህሪ ነች፡፡

## 3.4.3. ከአድማስ ባሻገር የሴት ገፀባህሪያት አሳሳል ትንተና

**<u>ሱዛን ሮዝ</u>**

**<u>አካላዊ አሳሳል</u>**

ቀይ አይኖቿ ትናንሽ ውብ ፀጉሯ ረጅም እንዲሁም የነጡ ጥርሶቿ ከሩቅ ሲታዩ ነጭ የሚመስሉ ቀርበው ሲያዩት ግን ሸሮ የሚመስሉ፡፡

ጭኗ ውርጭ ውስጥ እንደደረ ብረት የሚቀዘቅዝ ስትናደድ ከጉንጮ ላይ ያለዉ ደም ቁልቁል ወርዶ ቁንጅናዋ ባንዴ ፀሐይ ያልነካው በሽተኛ ይመስል የምትገረጣ የደም ስሮቿ እንደ ስምጥ አጥር የሚወጠሩ፡፡

**<u>ማህበራዊ አሳሳል</u>**

የሰላም ጓድ ልኡካን ባለደረባ የዋና ገጸ ባህሪው የአበራ የድሮ ፍቅረኛ ከመሆኗ ውጪ ስለማህበራዊ ህይወቷ የሚገልጽ ነገር የለም፡፡

**<u>ስነ-ልቦናዊ አሳሳል</u>**

ሱዛን ሮዝ ለየት ያለ ልምድ ያላት ገጽ ባህሪይ ነች፡፡ ሰውነቷ ያለሙዚቃ አይፍታታም፡፡ ሙዚቃ ካልሰማች የወሲብ ስሜቷ አይነሳሳም፡፡ ሙዚቃ ህይወቷ ነው፡፡ «ያለ ሙዚቃ አይሆንልኝም ሙዚቃ ስጠኝ ፍቅር ልስጥህ» ትላለች፡፡ ሙዚቃ ስትሰማ ህይወቷ ይታደሳል ሰውነቷ ሁሉ ይታዘዛታል፡፡ «ፍቅሬን ለወንድ አሳልፌ ከመስጠቴ በፊት ነብሴ ወደ ሙዚቃ አለም መግባት አለባት ከዚያ በኃላ ነፃነት ይሰማኛል ውስጤ እንደ ጽጌረዳ እንቡጥ ይከፋፈታል ለመስጠትም ሆን ለመቀበል ዝግጁ እሆናለሁ» ትላለች፡፡

ውድ የሆነ ነገር ትወዳለች ብልጫ ያለው ነገር የሚመርጥ ወንድ ያስደስታታል ወንዶችን ማሞላቀቅ

ትችልበታለች።

**ሞራላዊ አሳሳል**

ትናዳጅ ስትናደድ ስሜቷ ፊቷ ላይ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ስሜቷን ከጠበቁላት ግን በፍቅር የምትንከባከብ ገጸ ባህሪ ነች።

## ሉሊት

**አካላዊአሳሳል**

ሉሊት የውበት ድባብ የምትባል አይደለችም ግን ታስደነግጣለች ግንባሯ  አጭር ሆኖ በመጠኑ ስልክክ ብሎ የወረደዉ አፍንጫዋ ከስር ሲደርስ ወደ ላይ ይገለበጣል። አይኖቿ እንደፈርጥ ይንቦገቦጋሉ ከንፈሯ ሊፈነዳ የደረሰ የጽጌረዳ እምቡጥ ይመስላል አንገቷ ረጅም ትክሻዋ ክብ ነው። የምትቀባው ሽቶ ማዕዛ ከሩቅ ያውዳል።

**ማህበራዊ አሳሳል**

የአበራ ሚሰት ነች። እናቷ በልጅነቷ ነበር የሞተችባት የእንጀራ አባቷ ለብር ብሎ ይድራታል ባሏም ልጃገረድ አይደለችም ብሎ ፈታት። ከዚያ በኃላ ከተወለደችበት ሃገር ጠፍታ ወደ አዲስ አበባ መጣች የብቸኝነት ኑሮን ተያያዘችው። ብቻዋን እየሰራች ራሷን ታስተዳድራለች።

**ስነልቦናዊ አሳሳል**

በልጅነቷ በማታውቃቸው ወንዶች ስለተደፈረች እንጀራ አባቷ ለማታውቀው ሰው አሳልፎ ስለዳራት ባሏም ልጃገረድ አይደለሽም ብሎ ስላዋረዳት ለወንድ ልጅ ያላት አመለካከት የወረደ  ነው።ወንድ ልጅ ሁሉ ጨካኝ አረመኔ ነው ብላ ታስባለች። ወንዶችን ከስሯ ማሰገድ ደስ ይላታል። ለራሷ "ጫይም ጣኦት" የሚል ስያሜን ሰጥታለች። ወንዶች እግሯ ስር ካልሰገዱ ሰውነቷ አይታዘዝላትም በረዶ ነች። እነሱ ታዛዥ እሷ ደግሞ አዛዥ ስትሆን እጅግ ትደሰታለች፡

**ሞራላዊአሳሳል**

ለራሷ ያላት ግምት ከፍተኛ ነው። "ማንም ወንድ ሉሊትን ተራምዶ አይሄድም" የሚል አቋም አላት።  ሁሌም ራሷን ከፍ ታደርጋለች ሁሌም ወንዶችን አሽንፋ መኖር ትፈልጋለች።

## 3.5. ከእንስታዊነት ጽንስ ሀሳብ አንጻር ትንተና

ይህ ጥንታዊ ጸሁፍ የበአሉ ግርማ ልብ ወለዶች ከሆኑት መሀል ኦሮማይ ድራሲው እና ከአድማስ ባሻገር ዉስጥ ያሉ ሴት ገጸ ባህሪያትን ከእንስታዊነት አንጻር ያብራራል። አጥኝዋ እነዚህን መጽሐፍቶች ከእንስታዊነት አንጻር ለመተንተን በዋናነት ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎች ታነሳለች።

1. የሴት ወይም የወንድ ሃላፊነት ነው ተብለዉ የተቀመጡ ስራወች አሉ ?
2. የወንድ የበላይነት በምን መልኩ ተገልጸዋል ?
3. ገጸ ባህሪያት ሲሳሉ በማን እጅ ላይ ነው ?

### 3.5.1.ኦሮማይ ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና

ይህ ልብወለድ በ1979 አ/ም ታትሞ ለህዝብ የቀረበ ሲሆን በጊዜው የነበረውን የፖለቲካ አቋም እና የአኗኗር ሂደትን በደንብ ያስሳል። እዚህ ልብ ወለድ ዉስጥ የምናገኛቸው ሴት ገጸ ባህሪያት ሁለት ብቻ ናቸው። ደራሲው ይሄን ታሪክ የጻፈበት ጊዜ የደርግ ዘመን በመሆኑ በደርግ እና በሻዕቢያ ይደረጉ የነበሩ ፍልሚያወችን በሰፊዉ ይገልፃል። እነዚህ ሁለት ሴት ገጸ ባህሪያትን የሳላቸው አንዷን አዲስ አበባ ሌላኛዋን ደግሞ አስመራ ነው። በነሱ አማካኝነት በጊዜው የነበሩ ሴቶችን በደንብ ገልጸቸዋል።ይህን እንደመነሻ ካነሳን ጥናታዊ ጽሁፉ ስለሚያነሳው መሰረታዊ ጥያቄ እንመልከት

1. **<u>ሴት ወይም የወንድ ሃላፊነት ተብለው የተቀመጡ ስራወች አሉ ?</u>**

እዚህ ልብ ወለድ የሴት የወንድ ተብለው የተቀመጡ ሃላፊነቶችን በሰፊው እናያለን። በመጀመሪያ ሁለቱም ሴት ገጸ ባህሪያት በወንድ ስር ወይም የወንድ ጠባቂ ሆነው ተስለዋል። ህይወታቸው ከወንድ ጋር በጣም የተቆራኘ ነው። ፍቅረኞቻቸውን መጠበቅ ማስደሰት መስዋት መሆን በነሱ ምክንያት ህይወታቸውን ማዘበራረቅ ሲኖረዉ ይህ ሁሉ በህይወታቸው ሲከሰት የምናየው ደራሲው የነሱ ሃላፊነት አድርጎ ያስቀመጣቸው እነዚህ ነገሮችን ስለሆነ ነው። አብዛኛዉ የውጭውን ስራ የሚሰሩት ወንዶች ናቸው። ሮማንን እንደምሳሌ ብንወስዳት የእሷ ሃላፊነት ባሏ ሲሄድባት ቤት እየጠበቀች እና ቀን እየቆጠረች እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ሴት የቤቱን ስራ እንደምትሰራ እና ምንም አማራጭ ስለሌላት እየከፋትም ቢሆን ባሏን ማጽናት ብቻ ነበር።የባሏ ጸጋዬ ሃላፊነት ወጥቶ መስራት ነው።

2. **<u>የወንድ የበላይነት በምንመልኩ ተገልጸዋል?</u>**

እዚህ ታሪክ ላይ የምናገኛቸው ወንዶች ከስራቸው ጀምረን እስከ ፍቅር ህይወታቸው ስናይ ሁሉም የበላይነታቸውን ማረጋገጥ ሚፈልጉ የሴት ልጅ ነጻነትን የሚነፍጉ ናቸው። የፊያሜታ ጊላይን ህይወት ስንመለከት ከልጅነቷ ጀምሮ ክብረ ንጽህናዋን ያጣችው ያለፍላጎቷ በወንድ ተጽዕኖ ነዉ። እሷ ለወንዶች ያላት

አመለካከት መጥፎ ነው ፍላጎቷን ስለማያዳምጡ የራሳቸውን ስሜት ብቻ አስቀድመው ወደ አልጋ ስልሚጎትቷት ስትቀርባቸው ለሷ ሳያዝኑ አንዳንዶችም ቻዉ ሳይሏ ትጥለዋት ስለመሄዱ ስትቆጣቸው አጉል ወንድ ነን በሚል ስሜት ተሞልተው ቀንተው መውጫ መግቢያ ያሳጧታል ነጻነቷን ይነሷታል ልክ እንደ ግኡዝ እቃ የኔ ብቻ ነሽ ብለው ሊያዙ ይፈልጋሉ እነሱ የማይፈልጉትን ነገር አድርጋ ካገኙ የሚማቱም አጋጥመዋታል፡፡ ትዳራቸውን እና ልጆቻቸውን ትተው በማንአለብኝነት ስሜት ከእሷ ጋር ይመጣሉ እሷም ከዚህ ለማምለጥ ስትል ከአንዱ ጋር ከዛም አልሆንም ሲላት ከሌላኛው ጋር እየሆነች የብዙ ወንድ ጸባይ እንዳየች እና ወንዶች ሁሌም የበላይነታቸውን ለማሳየት ሲሉ ያደረሱባትን በደል በልብ ወለዱ ላይ መረዳት ይቻላል፡፡

ሮማን ጸጋዬን በጣም ተወደዋለች እሱ ግን እሷን ትቶ ሌላ የአስመራ ሴት አፍቅሮ ህልሟን ተስፋዋን እና ፍቅሯን ሲያኳስስ እናየዋለን፡፡ ይህን በማድረጉ ሲፀፀት እና እሷን ለመካስ ሲጥር አናይም፡፡ በመጨረሻ ልቧ እንደተሰበረ ታሪኩ ይደመደማል፡፡ ፊያሜታም በመጨረሻ ሰአት ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር ቢይዛትም ደስተኛ መሆን አልቻለችም፡፡ በጸጋዬ የስራ ሁኔታ ምክንያት ተገደለች ለሱ ስትል ህይወቷን አሳልፋ ሰጥታለች፡፡ ስለዚህ ሁለቱም ሴት ገጸ ባህሪያት ከወንድ እኩል ወይም የበላይ ሁነዉ ምንም ነገር ሲፈጸሙ አይታይም ደራሲው ደስታን አግኝተው እንዲኖሩ አልፈቀደላቸውም፡፡

3. <u>ገጸ ባህሪያት ሲሳሉ በማን እጅ ላይ ነው?</u>

ከላይ እንዳየነው የዚህ ልብ ወለድ ታሪክ  የወንድ የበላይነት የሰፈነበት  ነው ፡፡በፍቅር ህይወት በስራ አለም ባለስልጣን ደራሲወች ጋዜጠኞች ከፍተኛ አመራሮች የጦር ኃይሎች ሁሉም ሙያዎች ማለት በሚያስችል ሁኔታ የተያዙት በወንዶች ነው፡፡ከወንድ እኩል ስልጣን ላይ ያለች ወይም በበላይነት የምትመራ ተደርጋ የተሳለች ሴት ገጸ ባህሪ የለችም፡፡

ፊያሜታ ለፀጋዬ ስለ አስመራ ሴቶች ስትነግረው እንዲህ ትላለች ‹‹አባቴ ይሙት አሁን ምን ሀሳብ አለ ኢሰፓ እኮ ከመጣ ወዲህ በጉልበት የሚደፍረን የለም እንደልባችን  ለብሰን እና አጊጠን እንወጣለን፡፡ የሴቶች በስነ-ስርዓት መልበስ ማጌጥ እና መውጣት የሠላም ምልክት መሆኑን ታውቃለህ?›› ከዚህ ቃለተውኔት እንደምናየው ሴቶች ነፃነት የላቸዉም ሴቶች ለለበሱት እና ለዘነጡት ወንዶች ስልጣን ስላላቸው ብቻ አስገድደው እንደሚደፍሯቸዉ ማወቅ ይቻላል፡፡

## 3.5.2. ደራሲው ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና

### 1. የሴቶች ወይም የወንዶች ተብሎ የተቀመጠ ኃላፊነት አለ?

የዋና ገጸ በህሪውን የሲራክ እና የባለቤቱ ፅጌን ኃላፊነት ብንመለከት ፅጌ የቤት እመቤት ነች እቤት አትወጣም አትማርም አትዝናናም ፡፡ ወጥ መስራት ልጅ መንከባከብ ቤት ማፅዳት ቡና ማፍላት እንጀራ መጋገር የመሳሰሉት ቤት ውስጥ ስራዎች ሁሉ የእሷ እና የቤት ሠራተኛዋ ውባንች ሀላፊነት ናቸው፡፡

የሲራክ ሀላፊነት ደግሞ ስራ ቦታ ሄዶ ስራ ሰርቶ መምጣት ነው፡፡ የመንግስት ስራ ሰርቶ የሚያመጣው ብር ህይዎታቸውን ለመምራት አይበቃም በዚህ ላይ የድርሰት ስራው ለማሳተም ብሎ ያለ የሌለ ንብረታቸውን አውጥቶ በእዳ እንዲዘፈቁ አደረገ፡፡ የባለቤቱን ስሜት እንኳን አልጠበቀም አባወራ ስለሆነ እሱ ወስኖ እዳ ውስጥ አስገብቷታል ይህን እዳ ለመክፈል ግን ሁለቱም ተፍ ተፍ ይላሉ፡፡ሰብለን እና ባለቤቷን ዘመነን ስናወዳድር ደግሞ ሰብለ የመንግስት ስራ ብትሰራለች ልጆቿን የምትንከባከበው ወጥ የምትሰራው ቤት የምታጸዳው እሷ ነች ባጠቃላይ የቤት ውስጥ ሀላፊነት የእሷ ነው፡፡ ውጭ ሰርታ መጥታ በተጨማሪ ቤት ውስጥ ብቻዋን ትሰራለች ትልቅ ኃላፊነት ተሸክማለች፡፡ ዘመነ ውጭ ወጥቶ ስራ ይሰራል ብር ያመጣል የቤት ውስጥ ስራ የሱ ሀላፊነት አይደለም ልጆቹን እንኳን በመንከባከብ አያግዛትም ጭራሽ የምትሰራውን ወጥ አይጣፍጥም ሴት አይደለሽም ስትንዘላዘይ ነው የምትውይው እያለ ይዘልፋታል፡፡

## 2. <u>የወንድ የበላይነት በምን መልኩ ተገልፆል?</u>

ከላይ የተጠቀሱት ሲራክ እና ዘመነ ሁለቱም በሚስቶቻቸው ላይ የበላይነታቸውን የሚያሳዩ ሚስቶቻቸውን የማይንከባከቡ የራሳቸውን ህልም እና ስሜት ብቻ በማዳመጥ የሚስቶቻቸው ፍላጎት እረግጠው የሚኖሩ ባሎች ናቸው፡፡

ሲራክ ለፅጌ ሌላ ሴት ይደርብባታል፡፡ ማታ ከድርሰቱ ጋር ሲታገል አብሯት አይተኛም የሷን ስሜት አይጠብቅም ለራሱ ህልም ሲል እሷ መኖር የማትፈልገውን ህይወት እያኖራት ነው፡፡ መኖር የማትፈልግበት ሰፈር ውስጥ ደስ በማይል ኑሮ እንድትኖር ያስገድዳታል፡፡ እሷም አማራጭ ስለሌላት እየተጨቃጨቀች አብራዉ ትኖራለች፡፡

ዘመነ ሁሌም እየሰከረ እና በቅናት ድብን እያለ ሚስቱ ሰብለን በስድብ በዘለፋ በማንቆሸሽ እና በመደብደብ የሚደሰት በጉልበቱ እና በብሩ የሚያምን የገዛ ባለቤቱን ከገንዘብ ጋር የሚያወዳድር የእሷን ስራ የሚያጣጥል የወረደ ስብዕና አለው፡፡ ለዚህ ሀሳብ እንደ ማመሳከሪያ የሚሆነን የሰብለ ቃለተውኔት፡-

‹‹ሴት ነኝ ለዚያዉም ተራ ሴት አይደለሁም አይዞሽ በርች

የሚለኝ ጥሩ ስራዬን የሚያደንቅልኝ መጥፎም ከሰራው

ከስህተቴ እንድማር የሚያደርገኝ ከቤት እቃዎች ውስጥ

እንዱ አለመሆኔን የሚገነዘብልኝ ባል እፈልጋለሁ፡፡ አንተ ግን

ነጋ ጠባ ሞራሌን ልትገድል ነው የምትፈልገው ገረድ

ልታደርገኝ ነው የምትፈልገው ባሻህ አንተ ባሰኝህ ጊዜ

የምታገኛት እቃ አድርገህ ልትቆጥረኝ ነው የምትፈልገው

በቃኝ አንገፈገፈኝ በቃኝ፨(1972፡26)

ይህ የሰብለ ቃለ ተውኔት የባሏ የበላይነት ምን ያህል እንደጎዳት በመከፋት የተናገረችበት ነው።

3. <u>**ገጸ ባህሪያት ሲሳሉ ስልጣኑ በማን እጅ ላይ ነው።**</u>

ሴትን የሚበድሉት የሚደሰቱት ለስሜታቸው እና ለፍላጎታቸው የሚሯሯጡትን ሀብት ያላቸው እና ስራ ሰርተው ብር የሚያመጡት ወንዶች ናቸው። ምንም አይነት ሴት ከስልጣን ላይ የለችም በራሷ ጊዜ ሰርታ የምትመራ ተሰሚ የሆነች ከወንድ ጥገኛ ያልሆነች ሴት የለችም ውስጣቸው ብቃት እያለ እራሳቸውን ችለው መቆም እየቻሉ ሞራሉ እያላቸው በተለያየ ምክንያት ግን ከወንድ ጥገኛ ሆነው እንዲኖሩ ተደርገው ተስለዋል።

## 3.5.3. ከአድማስ ባሻገር ከእንስታዊነት አንጻር ትንተና

ይህ ልብ ወለድ የተፃፈው በ1962ዓምሲሆን የበአሉ ግርማ የመጀመሪያ ልብ ወለድ መፅሀፍ ነው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ዋና ገጸ ባህሪዉ አበራ በስራው ደስተኛ እንዳልሆነ እና የሚፈልገውን ነገር ማወቅ ስለሚከብደው በራሱ በቤተሰቦቹ በፍቅረኛው እና በጓደኛው ህይወት ውስጥ የሚመጣውን መዘዝ በጥልቀት ይተርካል።

1. <u>**የሴት ወይም የወንድ ተብሎ የተቀመጡ ስራዎች አሉ?**</u>

በግልጽ ይህ የሴት ነው ይህ የወንድ ነው ተብለው ባይቀመጡም በተለያየ መንገድ የቤት ውስጥ ስራ እንደተለመደው የሴት ሀላፊነት እንደሆነ እና የወንድ ሀላፊነት ደግሞ የበላይ አባወራ ሆኖ ማስተዳደር እንደሆነ ተገልፆአል።

2. <u>**የወንድ የበላይነት በምን መልኩ ተገልፆል?**</u>

ሉሊትን ስናይ በልጅነቷ እናቷ ከሞተች በኋላ በማታውቃቸው ወንዶች መደፈሯ በአባቷ ተገዳ ማግባቷ ባሏ ክብሯን አራክሶ እቤት መባረሯን እናያለን። ከልጅነት እድሜዋ ጀምሮ የወንዶችን የበላይነት ተቃወማለች እነሱን ከስሯ ዝቅ ማድረግ ትፈልጋለች። ከዚህ መፅሀፍ የምናገኛቸው ሴተኛ አዳሪዎችንም ስንመለከት አበራ እና ጓደኛው ጊዜያዊ ሰሜታቸውን ለማብረድ ገንዘብ ከፍለው ሊጠቀሙባቸው ነው የሚፈልጓቸው። አበራ በሉሊት ተናዶ ሰሜታዊ ሲሆን ስሜቱን ለማረጋጋት እነሱ ጋር ሲሄድ እናያለን። ስለዚህ እሱም የበላይ ሆኖ

ተጠቅሞባቸዋል። ጋሽ አባተም መውለድ ስለማይችል ሚስቱ ላይ ቁጭቱን ሲወጣባት ሁሌ እየሰከረ  ዘረ-ቢስ ሆኘ ቀረሁ እያለ ስሜቷን ሲጎዳት እናያለን።

3. **<u>ገፀ ባህሪያት ሲሳሉ ስልጣኑ በማን እጅ ነው?</u>**

ከላይ እንደተዘረዘሩት ሁለቱ ልብ ወለዶች እዚህ ላይም የትኛዋም ሴት የበላይ ሆና ስትሰራ አይታይም። ስልጣኑ ሙሉ በሙሉ የወንዶች ነው ። ሁሉም ቦታወንዶች የበላይ ሆነዉ ተስለዋል።

# ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

### 4.1. ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ በበአሉ ግርማ ሶስት ልብ ወለድ ድርሰቶች ዉስጥ የተሳሉ ሴት ገፀ ባህሪያት ተቃኝተዋል። በሀገራችን ማህበረሰብ በስርአተ-ፆታ አኳያ የተሳሳተ አመለካከት እና ድርጊት በስነጽሁፍ ስራዎች ላይም እንዴት ታይቷል እንዴት ተስለዋል በማለት ተመርምረዋል።

በዚህም ሴት ገፀ ባህሪያት ሁሉም እርስ በእርሳቸው ካሉበት የኑሮ ሁኔታ ከቤተሰብ ደረጃ ከትምህርት ደረጃ ከዕድሜ ከስራ እና ከመሳሰሉት አንፃር እንስታዊነት እንዴት እንዳንጸባረቁ እና ከማህበራዊ አካላዊ ሞራላዊ እና ስነልቦናዊ የአሳሳል ደረጃ እንዴት እንደተሳለሉ ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል።

አጥኝዋ በምታጠናበት ወቅት የበአሉ ግርማ የራሱ የሆኑ የገጸ ባህሪያት አቀራረፅ ስልት እንዳለው ማየት ችላለች። ይህ በመሆኑ ድርሰቶቹ የራሳቸው የሆነ ባህሪ እንዲኖራቸው አድርጎታል። አንድ ሰው ይወለዳል ያድጋል ይሞታል እንደሚባለው ሁሉ አንድ ልብ ወለድም ሊያድግና ሊሞት የሚችለው በውስጡ ነብስ ዘርተው በሚንቀሳቀሱት ገጸ ባህሪያት አማካኝነት ነው። የበአሉ ግርማ ኦሮማይ፣ ደራሲው እና ከአድማስ ባሻገር ልብ ወለድ ዉስጥ ያሉ ሴቶች ከገፀ ባህሪያት አሳሳል አንጻር ጥሩ በሚባል ሁኔታ ተስለዉ ይገኛሉ። ነገርግን ሴት ገጸ ባህሪያትን ከወንድ ገጸ ባህሪያት በቁጥርም ሆነ በተሰጣቸው ሚና ዝቅ አድርጎ ስሏቸዋል። ወጣ ያለ ወይም ጥልቅ ሀላፊነት ሰጥቷቸው ወይም ከውበታቸው በዘለለ ከወንድ እኩል ስራ ሰጥቶ እንዲወስኑ እና እራሳቸውን ችለው እንዲኖሩ አልፈቀደላቸውም እንዲሁም ሶስቱ ልቦለዶች ላይ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያቶቹ ከአራቱ የገፀ ባህሪ አሳሳል አንፃር ተመሳሳይነት እንዲኖራቸው አድርጎ ስሏቸዋል።

### 4.2. የመፍትሄ ሀሳብ

ልብ ወለድ የገሀዱ አለም ነፀብራቅ እንደመሆኑ መጠን የሰው ልጅ ሀዘኑን ደስታውን ምኞቱን እና የውስጥ ፍላጎቱን ሁሉ የሚያንጸባርቅበት የስነ- ፅሁፍ ዘርፍ ነው። በመሆኑም ደራሲያን ልብ ወለድ ሲጽፉ የሰውን ልጅ ለማስተማር እና መልዕክት ለማስተላለፍ እንደመሆኑ መጠን የበአሉ ግርማ ስራ ላይ እንደተስተዋለው ነው።

አጥኝዋ የሴትን ልጅ ሚና አሳንሶ እና ከወንድ ስር አድርጎ ገጸ ባህሪ መሳል ትክክል አይደለም ብላ ታምናለች። በመሆኑም የሴት እና የወንድን እኩል ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተለያዩ የመፍትሄ እርመጃዎች እንዲወሰዱ ለእንስታዊነት ፅንስ ሀሳብ ትኩረት ተሰጥቶት በስፋት እንዲሰራ ማህበረሰቡ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት

እንዲቀየር ሴቶች ለመብታቸው መሟገት እንዲችሉ ደራሲዎቻችን ይህን ተረድተው እኩልነትን የሚያሳዩ እና የሚያስተምሩ ስራዎችን መስራት ተገቢ ነዉ፡፡ ስነጥበብ ደግሞ ከሌሎች ዘርፎች ሁሉ በተሻለ ለሰው ልጅ ስሜት ቅርብ በመሆኑ በትኩረት ቢሰራበት በአጭር ጊዜ ውስጥ አስደሳች ለውጥ ማምጣት እንደሚችል አጥኝዋ ታምናለች፡፡

## 4.3. ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ

1. Patriarchy is a system of society or government in which the father or eldest male is head of family and descent is reckoned through the male line.
2. Feminism is the advocacy of women's right on the ground of the equality of the sexes.
3. Feminism is the belief in social, economic and political equality of the sexes.

## 4.4. ዋቢ መጽሀፍት


ሚካኤል ልዑል ሰገድ፡፡ የፊልም ጽሁፍ ፡፡ አዲስ አበባ ፣ ብራና ማተሚያ ቤት ፣2006ዓም፡፡

አማረ ማሞ፡፡ የልብ ወልድ ድርሰት አጻጻፍ፡፡ አዲስ አበባ ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት ፣1997፡፡

ካቢኒ መኮነን፡፡ የገጸ ባህሪያት አሳሳል በየጠፍ ከዋክብት ረጅም ልብ ወለድ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋ ጥናት ተቋም ፣ ሰኔ 2001 ዓ/ም

ዘሪሁን አሰፋዉ፡፡ የስነጽሁፍ መሰረታዉያን፡፡ አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 2007ዓም

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሰማንያ አሀዱ መጽሀፍ ቅዱስ ፡፡በኢትዮጵያ መጽሀፍ ቅዱስ ማህበር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ታተመ፣2002ዓ/ም፡፡

ዮናስ እንዳልካቸዉ ፡፡ የዋና ዋና ገፀ ባህሪያት ትንተና በባዶ እግር ተዉኔት ፡፡ለጎንደር ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሞያ፣ ሰኔ 2010 ዓ/ም

ደበበ ሰይፉ፡፡ የቴያትር ጥበብ ከጽሀፈ ተዉኔት አንፃር፣ አዲስ አበባ ፣ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1973ዓም፡፡

Annete kolodny. Some notes on defining a feminist litrary criticism. the university of Chicago press jornal, 1975

Elinore Burkt .feminism society. Britanica article, February 8, 2019

Nuri atiqahe.an analaysis of the main character through feminism approach in the novel Lucia Lucia by Adrian trigani. Jakareta, 2010

Oxefored.English oxfored living dictionaries

Peterburi tee. A simple guide to feminist theory and criticism.

Pomi Ayalew. Ethiopian feminist movement and the role of setaweet. Pambazuka news voice for freedom and justice jornal, November 17, 2016.

Rubina mandokhil. Feminist critique of the character dezidemona in shakespear's 'othello'.English language and literature studies, 2015.

www.wikipedia.org . Feminist movement and the ideology.